Wellpoint District of Columbia, Inc. የዲሲ ጤናማ ቤተሰቦች ፕሮግራም (DC Healthy Families Program) እና የስደተኛ ልጆች ፕሮግራም (Immigrant Children's Program, ICP)

# የተመዝጋቢ የመመሪያ መጽሃፍ

Wellpoint
District of Columbia

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት ሊደውሉልን፣ ወይም ቢሯችን ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 መምጣት ይችላሉ። እንዴት እንደሚያገኙን አቅጣጫውን ለማወቅ፣ ይደውሉ **በ833-359-1384 (TTY 711)**።


Wellpoint District of Columbia, Inc.
609 H Street NE
Ste. 200
Washington, DC 20002


የቢሮ የስራ ሰዓታት፥ ከጧት 8:00 እስከ ምሽት 6:00

**202-548-6700**
**833-359-1384 (TTY 711)**

Do you need help with your healthcare, talking with us, or reading what we send you? We provide our materials in other languages and formats at no cost. Call us toll-free at 833-359-1384 (TTY 711). English

¿Necesita ayuda con el cuidado de la salud, para hablar con nosotros o para leer lo que le enviamos? Ofrecemos nuestros materiales en otros idiomas y formatos sin costo alguno. Llame a nuestra línea gratuita al 833-359-1384 (TTY 711). Spanish

በእርስዎ የጤና ክብካቤ ላይ፣ ከእኛ ጋር በመነጋገር ላይ፣ ወይም እኛ የምንልክልዎትን ነገሮች በማንበብ ላይ እገዛ ያስፈልግዎታል? የእኛን የሚነበቡ ነገሮች በሌሎች ቋንቋዎች እና ቅርጸቶች ምንም ወጪ ሳያስከትልብዎት እንሰጥዎታለን። በነጻ የስልክ መሥመር በስልክ ቊጥር 833-359-1384 (TTY 711) ይደውሉልን። Amharic

건강 관리에 도움이 필요하십니까? 아니면 저희와 연락하시거나, 보내드리는 자료를 읽는 데 도움이 필요하십니까? 자료를 다른 언어 및 형식으로 무료로 제공해드립니다. 저희에게 833-359-1384 (TTY 711) 번으로 연락해 주십시오. Korean

您在醫療保健方面、與我們交流或閱讀我們寄送的材料時是否需要幫助？我們可免費提供其他語言和格式的材料。請撥打我們的免費電話 833-359-1384 (TTY 711)。Chinese Traditional

Avez-vous besoin d’aide pour vos soins de santé, pour parler avec nous ou pour lire ce que nous vous avons envoyé ? Nous pouvons fournir gratuitement nos documents dans d’autres langues et formats. Appelez notre numéro gratuit 833-359-1384 (TTY 711). French

Quý vị có cần trợ giúp liên quan tới chăm sóc sức khỏe, nói chuyện với chúng tôi, hoặc đọc nội dung chúng tôi gửi cho quý vị không? Chúng tôi có cung cấp tài liệu bằng các ngôn ngữ và định dạng khác mà không tính phí. Hãy gọi chúng tôi theo số điện thoại miễn cước 833-359-1384 (TTY 711). Vietnamese

N̂ a jlȧ bò mamȧɛ̀ kȯ n̂-ȧ fuɛjì-ȧ jȧ ėti nlɔnlɔɛ-ȧ tèh bò, mɔ̀ɔ̀ bê yė-lė âmô bò wlu, mɔ̀ɔ̀ bê yė dɛ nė â a mua mû bò dlo slɛ̀? Dɛ wɛ̀ nė â a clėa, â a po-lė i dakɔ̇+ tê-ȧ win klì kà nė i a mua i-ȧ nyati wɔnwɔ̇ɛ̀n nu, ɛ se pɛnȯ kpȯh. Dȧ âmô, ɛ se pɛnȯ kpȯh ne 833-359-1384 (TTY 711). Kru

ヘルスケアの受診、ご相談時の会話、配布物の読解にお困りではありませんか？当院では無料の翻訳版資料をご用意しております。無料ダイアル 833-359-1384 (TTY 711) までお電話ください。 Japanese

Вам нужна помощь в получении медицинских услуг, вы хотите поговорить с нами или не можете прочитать присланные вам материалы? Наши материалы можно бесплатно получить на других языках и в другом формате. Позвоните нам по бесплатному номеру 833-359-1384 (TTY 711). Russian

Necessita de ajuda com a sua assistência médica, para falar connosco ou para ler o que lhe enviamos? Fornecemos os nossos materiais noutros idiomas e noutros formatos, sem qualquer custo. Ligue-nos gratuitamente para 833-359-1384 (TTY 711). Portuguese

Ha bisogno di aiuto con la sua assistenza sanitaria, per parlare con noi o per leggere ciò che le abbiamo inviato? I nostri materiali sono disponibili in altre lingue e formati senza alcun costo. Può contattarci gratuitamente al numero 833-359-1384 (TTY 711). Italian

Kailangan ba ninyo ng tulong sa inyong pangangalagang pangkalusugan, sa pakikipag-usap sa amin, o sa pagbabasa ng aming ipinadadala sa inyo? Ipinagkakaloob namin ang aming mga materyal sa iba pang mga wika at format nang walang bayad. Tawagan kami nang toll free sa 833-359-1384 (TTY 711). Tagalog

**คุณต้องการความช่วยเหลือในด้านการดูแลสุขภาพของคุณ พูดคุยกับเรา หรืออ่านสิ่งที่เราจัดส่งให้คุณหรือไม่ เราจัดส่งสื่อของเราเป็นภาษาและรูปแบบอื่นๆ โดยไม่มีค่าใช้จ่าย โทรหาเราฟรีที่** 833-359-1384 (TTY 711). Thai

Ị chọrọ enyemaka na nlekọta ahụike gị, ịgwa anyị okwu, ma ọ bụ ịgụ ihe anyị zitere gị? Anyị na enye ihe anyị n'asụsụ na nhazi ndị ọzọ na akwụghị ụgwọ ọ bụla. Kpọọ anyị n'efu na 833-359-1384 (TTY 711). Igbo

Njẹ́ o nílò ìrànlọ́wọ́ nípa ìtọ́jú ìlera rẹ, ní bíbá wa sọ̀rọ̀, àbí kíkà ohun tí a fi ránṣẹ́ sí ọ? A npèsè àwọn nnkan wa ní àwọn èdè míràn àti ní irú míràn láì díyelé. Pè wá lọ́fẹ̀ẹ́ ní 833-359-1384 (TTY 711). Yoruba

আপনার কি আপনার স্বাস্থ্য পরিচর্যা, আমাদের সঙ্গে কথা বলার ক্ষেত্রে অথবা আমরা আপনাকে যা পাঠায় তা পড়তে সহায়তার প্রয়োজন? আমরা অন্য ভাষা ও ফর্ম্যাটে বিনামূল্যে আমাদের সামগ্রী প্রদান করি। আমাদের টোল-ফ্রি নম্বর 833-359-1384 (TTY 711) এ ফোন করুন। Bengali

Benötigen Sie Hilfe bezüglich Ihrer Gesundheitsversorgung, möchten Sie mit uns sprechen oder haben Sie Probleme, die von uns zugesandten Materialien zu verstehen? Wir stellen unsere Materialien auch in anderen Sprachen und Formaten kostenfrei zur Verfügung. Sie erreichen uns gebührenfrei unter 833-359-1384 (TTY 711). German

**ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስለ እርስዎ MCP ጥያቄዎች ካሉዎት፥ | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 833-359-1384 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣<br>7 ቀናት በሳምንት |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣<br>7 ቀናት በሳምንት |
| የሐኪምዎ ቢሮ ከተዘጋ በኋላ ህክምና ካስፈለገዎት፥ | የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) | 833-359-1384 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣<br>7 ቀናት በሳምንት |
| | TTY/TDD የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) | 711 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣<br>7 ቀናት በሳምንት |
| በ 24 ሰዓታት ውስጥ ሐኪም ማየት የሚያስፈልግዎ ከሆነ ("አስቸኳይ ሕክምና")፥ | የእርስዎ PCP ቢሮ | (የእርስዎን የ PCP መረጃ እዚህ ይሙሉ) | |
| | የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) | 833-359-1384 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት |
| ወደ ቀጠሮ ለመሄድ ትራንስፖርት ካስፈለገዎት፥ | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | የህክምና ትራንስፖርት አስተዳደር (MTM)<br>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት<br>888-828-1081 (TTY 711) (ከክፍያ ነፃ) | |
| የባህሪ ጤና እንክብካቤ ከፈለጉ ወይም የባህሪ ጤና ጥያቄ ካለዎት፥ | የእርስዎ PCP ቢሮ | የDC የባህርይ ጤና ተደራሽነት መምሪያ የስልክ መስመር ላይ በ888-793-4357፣ 24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት። | |
| | የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) | 833-359-1384 (ከክፍያ-ነፃ) | 24 ሰዓት በቀን፣<br>7 ቀናት በሳምንት |
| ቋንቋዎን መናገር የሚችል ሰው ከፈለጉ ወይም መስማት የተሳነዎ ከሆኑ፥ | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 833-359-1384 (ከክፍያ-ነፃ) | ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8:00 እስከ ምሽት 6:00 ሰዓት |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ከክፍያ-ነፃ) | ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8:00 እስከ ምሽት 6:00 ሰዓት |
| የጥርስ ህክምና ጥያቄዎች፥ | Avesis (አቬሲስ) | 833-554-1012 | ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 7 እስከ ምሽት 8 ሰዓት |
| የዓይን ህክምና ጥያቄዎች፥ | Avesis (አቬሲስ) | 833-554-1012 | ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 7 እስከ ምሽት 8 ሰዓት |
| ለድንገተኛ ሁኔታ፣ ወደ 911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ | | | |

**የግል መረጃ**

የእኔ የMedicaid ID ቁጥር፥

---

የእኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP)፥

---

የእኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥

---

የእኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ፥

---

የልጅ የMedicaid መታወቂያ ቁጥር፥

---

---

---

የልጅ/ልጆች ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP)፥

---

የልጅ/ልጆች ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥

---

የልጅ/ልጆች ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ፥

---

የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP)፥

---

የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) አድራሻ፥

---

የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) ስልክ፥

---

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP)፥

---

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)አድራሻ ፥

---

የልጅ/ልጆች ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) ስልክ፥

---

የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ፥

---

የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ አድራሻ፥

የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ ስልክ፥

የልጅ/የልጆች ባህሪ ጤና አቅራቢ፡

የልጅ/የልጆች ባህሪ ጤና አቅራቢ አድራሻ፥

የልጅ/የልጆች ባህሪ ጤና አቅራቢ ስልክ፥

## ማውጫ


*ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች* ............................................................ *3*

ይህ የመመሪያ መጽሃፍ እንዴት እንደሚሰራ ............................................................ 9

ይህ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል............................................................ 9

*ግዴታዎችዎ* ............................................................ *11*

*የእርስዎ የተመዝጋቢ ID ካርድ* ............................................................ *12*

*የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)* ............................................................ *13*

የእርስዎን PCP ይምረጡ ............................................................ 13

የእርስዎን PCP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ............................................................ 14

*የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)* ............................................................ *14*

የእርስዎን PDP መምረጥ ............................................................ 14

የእርስዎን PDP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ............................................................ 14

*መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና* ............................................................ *15*

መደበኛ ህክምና ............................................................ 15

አስቸኳይ ህክምና............................................................ 15

የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና ............................................................ 15

*ከከተማ ውጭ ሲሆኑ የሚሰጥ እንክብካቤ* ............................................................ *15*

*ከአውታረ-መረብ ውስጥ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች* ............................................................ *16*

*ቀጠሮ ማስያዝ* ............................................................ *17*

የእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ ............................................................ 17

ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ............................................................ 17

የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት ............................................................ 17

ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? ............................................................ 17

*የድጋፍ አገልግሎቶች* ............................................................ *18*

የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/መስማት እና ማየት ለተሳናቸው ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች ............................................................ 18

*የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራሎች* ............................................................ *19*

የስፔሺያሊቲ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ............................................................ 19

የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች............................................................ 19

የባህሪ ጤና (የአእምሮ ጤና ወይም የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መታወክ አገልግሎቶች) ............................................................ 20

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ............................................................ 21

የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች ............................................................ 22

በሽታ መቆጣጠር ............................................................ 23

የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች....24

*አዋቂ ሰዎችን ከመታመም የሚከላከሉ አገልግሎቶች....24*

የክትትል ምርመራዎች ምክረሀሳቦች ("ማጣሪያዎች")....24

የመከላከል የምክር አገልግሎት....24

የአዋቂ ክትባቶች....25

*እርግዝና....25*

የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ ሕክምና....25

*የልጅዎ ጤና....26*

የHealthCheck ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራም ለልጆች (EPSDT)....26

የስደተኛ ቤተሰብ ልጆች ፕሮግራም....31

የልጅዎ የጥርስ ሕክምና....31

ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ያላቸው ህጻናት....32

የIDEA ፕሮግራም....32

ክትባቶች (መርፌዎች) ለልጆች እና ወጣቶች....34

*የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች....35*

ሽፋን የሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች በWellpoint DC....35

ክፍያቸውን የማንሸፍነው አገልግሎቶች....41

*የህክምና ሽግግር....41*

*ማወቅ ያለብዎ ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች....42*

ቦታ ከቀየርኩ ምን ማድረግ ይኖርብኛል....42

ህጻን ልጅ ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ....42

ህጻን ልጅ በማደጎ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ....42

ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ....42

የእኔን MCP እንዴት መቀየር እንደምችል....42

ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ሲደርሰኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ....43

ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች መክፈል....43

ሌላ መድን ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ....43

ማጭበርበር ምንድን ነው?....44

የሐኪም (ዶክተር) የጥቅማጥቅም እቅድ መግለጫ....44

*ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች....45*

ቅሬታዎች....45

ይግባኞች....45

ፍትሃዊ ችሎቶች....45

**የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት....46**
**በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሎት መብቶች....46**
***የግላዊነት ልምምዶች ማስታወቂያ.... 47***
**የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ ....50**
***ትርጉሞች.... 52***

**እንኳን ወደ Wellpoint DC በደህና መጡ።**

Wellpoint District of Columbia, Inc.ን እንደ የጤና እቅድዎ ስለመረጡ እናመሰግናለን። የዲስትሪክት Medicaid እና የ CHIP ተመዝጋቢዎችን በዲሲ ጤናማ ቤተሰቦች እና የስደተኛ ልጆች ፕሮግራሞች አማካኝነት በማገልገላችን ኩራት ይሰማናል።

ይህ የተመዝጋቢ መመሪያ መጽሐፍ ስለ Wellpoint DC እና የጤና እቅድዎ እንዴት እንደሚሰራ ጠቃሚ መረጃ አለው። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት። እንደ Wellpoint DC ተመዝጋቢ፣ መደበኛ Medicaid የሚሸፍናቸውን ሁሉንም መደበኛ ጥቅማጥቅሞች እንደ የሐኪም ጉብኝት፣ ላቦራቶሪ እና ኤክስሬይ፣ ክትባቶች፣ እንዲሁም ለጤናማ ኑሮ እና ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎ የሚያግዙ ተጨማሪ እገዛዎች ይኖርዎታል።

በየወሩ፣ Wellpoint DC አዲስ የተመዝጋቢ ገለጻ (ኦሪየንቴሽን) ያዘጋጃል። ይህ ስለ Wellpoint DC ጥቅማጥቅሞችዎ የበለጠ የሚማሩበት ሌላ መንገድ ነው። በገለጻው ወቅት፣ ለጥያቄዎችዎ መልስ ለማግኘት ከቡድናችን አባል ጋር መነጋገር ይችላሉ። ከእኛ ጋር አሁኑኑ መነጋገር ይፈልጋሉ? እኛ አንድ መጫን ወይም ስልክ መደወል ብቻ ርቀን እንገኛለን። ወደ መለያዎ (አካውንትዎ) ይግቡ ወይም በመስመር ላይ (ኦንላይን) ይመዝገቡ፣ በ**wellpoint.com/dc/medicaid**። ደህንነቱ የተጠበቀ የጽሁፍ መልእክት ይላኩልን ወይም ለመልሶ-መደወል ቀጠሮ ያስይዙ። ወይም ለእኛ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ቡድን በ**833-359-1384 (TTY 711)**፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 ይደውሉ፣ ወይም ወደ DCenrollees@wellpoint.com ኢሜይል ይላኩ። እኛ እዚህ ያለነው እርስዎን በእያንዳንዱ እርምጃ ለማገዝ ነው።

**ይህ የመመሪያ መጽሃፍ እንዴት እንደሚሰራ**

Wellpoint DC የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ ማግኘት እንዲችሉ ለማገዝ በColumbia ዲስትሪክት የሚከፈል ቁጥጥር የሚደረግበት የህክምና እቅድ ነው። በዚህ የመምሪያ መጽሃፍ፣ እኛ Wellpoint DC እንዴት እንደሚሰራ፣ ሐኪሞችን እንዴት እንደሚያገኙ፣ ወደኛ እንዴት መደወል እንደሚችሉ፣ እና እኛ ስለምንከፍላቸው ነገሮች እንነግርዎታለን። በጤና ህክምና እና በሐኪም የሚገለጹ ቃላት አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው። በትርጉሞች ክፍል፣ የእነዚህን ቃላት ፍቺ በዚህ መጽሃፍ ጀርባ ላይ አብራርተናል።

በዚህ መጽሃፍ ስላነበቡት ነገሮች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወይም ስለ Wellpoint DC ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ለWellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ**833-359-1384 (TTY 711)** መደወል ወይም **wellpoint.com/dc/medicaid** መጎብኘት ይችላሉ፣ እና እኛ እርስዎን ለማገዝ የተቻለንን እናደርጋለን።

**ይህ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል**

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ የሚከተሉትን ይነግርዎታል፥

- የጤና እንክብካቤን እንዴት እንደሚያገኙ
- በWellpoint DC ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶችዎ
- በWellpoint DC ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች
- ዋና የህክምና አቅራቢዎን እና ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢዎን (የእርስዎ PCP ወይም PDP) እንዴት መምረጥ እንደሚቻል
- ሲታመሙ ምን ማድረግ እንዳለብዎ
- ቅሬታ ካለዎት ወይም በWellpoint DC ውሳኔ ማስለወጥ (ይግባኝ) ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ Wellpoint DC እንደሚሰራ መሰረታዊ መረጃ ይሰጥዎታል። ማንኛውም ጥያቄዎች ካሎት እባክዎ ወደ Wellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በማንኛውም ጊዜ፣ 24 ሰዓት በቀን እና 7 ቀናት በሳምንት ይደውሉ።

**መብቶችዎ**

- ከሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች ጋር ሲያወሩ፣ ሚስጥራዊ መሆኑን ማወቅ
- በሚረዱት ቋንቋ በሽታው ወይም ሕክምናው እንዲገለጽልዎ መደረግ
- ስለ ሕክምናዎ በሚደረጉ ውሳኔዎች መሳተፍ፣ ሕክምና ያለመቀበል መብትን ጨምሮ
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ የተሟላ፣ ግልጽ እና ለመረዳት የሚቻል የሕክምና አማራጮችን እና የእያንዳንዱን አማራጭ አደጋ ማብራሪያ ማግኘት
- እንክብካቤ ወይም ሕክምና ማግኘት አለመፍቀድ
- ለማስገደድ፣ ለዲስፒሊን፣ ለምቾት፣ ወይም ለበቀል ዓላማ ከሚደረጉ ማንኛውም ገደቦች ወይም የመገለል ሁኔታዎች ነጻ መሆን
- የሕክምና ሪከርዶችዎን ማየት እና ቅጂ ማግኘት እንዲሁም ስህተት ካለበት እንዲሻሻል ወይም እንዲቀየር የመጠየቅ
- ያሉትን እና ለእርስዎ ተደራሽ የሆኑትን የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜ ማግኘት
- ብቁ የሆነ PCP/PDP ከWellpoint DC መረብ(ኔትዎርክ) ውስጥ መምረጥ እና የእርስዎን PCP/PDP መቀየር
- ስላገኙት ሕክምና ቅሬታ ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት
- Wellpoint DC አገልግሎት ወይም እቃ በመከልከል፣ በመቀነስ ወይም በማቋረጥ ትክክል አይደለም ብለው ካመኑ፣ ይግባኝ ወይም ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ
- ከሚመርጡት አቅራቢ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶችን ማግኘት
- ያለ አላስፈላጊ መዘግየት የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት
- በአውታረ-መረቡ ውስጥ ካለ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ፣ ከመረብ ውጭ ከሆነ፣ ብቁ ከሆነ የጤና ሕክምና ባለሞያ፣ እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ፣ ሁለተኛ አስተያየት ማግኘት
- የቀደመ መመሪያዎች ላይ መረጃ ማግኘት እና ማንኛውም የህይወት ማቆያ ሕክምናን ያለማግኘት ወይም ማግኘት መቀጠልን መምረጥ
- የWellpoint DC የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ እና/ወይም የአቅራቢ ማውጫ ቅጂን ማግኘት
- አዲስ የሕክምና እቅድ እስኪያገኙ ድረስ አሁን እያገኙ ያለውን ሕክምና ማግኘት መቀጠል
- የቃል ትርጉም እና የትርጉም አገልግሎቶችን ያለ ምንም ወጪ መቀበል
- የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን ማግኘትን አለመቀበል
- ያለ ምንም ወጪ የትራንስፖርት አገልግሎት መቀበል
- የቀደመ ፈቃድ ሂደቶች ላይ ማብራሪያ ማግኘት
- ስለ የWellpoint DC የገንዘብ ሁኔታ እና ለሐኪሞቻችን ክፍያ ስለምንፈጽምበት ማንኛውም ልዩ ዘዴዎች መረጃ ማግኘት
- የደምበኛ እርካታ የዳሰሳ ጥናቶች ማጠቃለያዎችን ማግኘት
- በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶችን በተመለከተ የWellpoint DC “በተጻፈው መሰረት ይስጡ” የሚል ፖሊሲ ማግኘት
- ሽፋን ያላቸውን የሁሉንም መድሃኒቶች ዝርዝር ማግኘት

**የሚከተለው መብት አለዎት፥**

ሰብዓዊነትዎን እና የግል ነጻነት መብቶን ባከበረ መልኩ በክብር መታከም

**ግዴታዎችዎ**

የሚከተሉት ግዴታዎች አሉብዎ፥

- ህክምና የሚሰጥዎትን ሰዎች በአክብሮት እና በክብር መያዝ
- የDC Medicaid የተቀናጀ የሕክምና ፕሮግራም እና የWellpoint DC ህጎችን ማክበር
- ሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች የሚሰጥዎትን መመሪያዎች መተግበር
- በተያዙት ቀጠሮዎች መገኘት
- ቀጠሮውን መሰረዝ ካለብዎ ቢያንስ ከ24 ሰዓታት በፊት ለሐኪምዎ መንገር
- የሐኪምዎ ትእዛዝ ካልገባዎ ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ
- ድንገተኛ ሕክምና ሲያፈልግዎ ብቻ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ
- ጤናዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለ ሚችሉ የሕክምና እና የግል ችግሮች ለእርስዎ PCP/PDP መንገር
- እርስዎ ወይም የቤተሰብ ተመዝጋቢ ሌላ የጤና መድን ካላችሁ ወይም የአድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጥ ካለ፣ ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና Wellpoint DC ሪፖርት ማድረግ
- በቤተሰብዎ ውስጥ ማንኛውም ለውጥ ካለ (ማለትም፥ ሞት፣ ወሊድ፣ ወዘተ) ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና Wellpoint DC ሪፖርት ማድረግ
- የጤና ችግሮችዎን ለመረዳት መሞከር እና የሕክምና ግቦች ዝግጅት ላይ መሳተፍ
- ሐኪምዎ ከዚህ በፊት እርስዎን ካከሙ አቅራቢዎች የሕክምና ሪከርዶችዎን እንዲያገኙ ማገዝ
- በአደጋ ምክንያት ወይም ሥራ ላይ ከተጎዱ ለWellpoint DC ማሳወቅ

## <u>የእርስዎ የተመዝጋቢ ID ካርድ</u>


ዋና የሕክምና አቅራቢ (PCP) አንድ ጊዜ ከተመደበልዎ በኋላ፣ የተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድ በፖስታ እንልክልዎታለን። ይህ ካርድ የእርስዎ ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች፣ የመድሃኒት መደብሮች፣ እና ሌሎች እርስዎ የWellpoint DC ተመዝጋቢ መሆንዎን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። እባክዎ በተመዝጋቢ የመታወቂያ ካርድዎ ላይ ያለው መረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። ማንኛውም ችግሮች ካሉ፣ ወይም ካርድዎ ከጠፋብዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። እያንዳንዱ የWellpoint DC ተመዝጋቢ የራሳቸው ካርድ አላቸው። በተጨማሪ የእርስዎም ልጆች የራሳቸው ካርድ ይኖራቸዋል። እንዳይጠፉ የልጆችዎን ካርድ እርስዎ መያዝ አለብዎ። የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ማንኛውም ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ በህግ የተከለከለ ነው።

### የተመዝጋቢ ID ካርድዎ ይህን ይመስላል፥

### የካርዱ ፊትለፊት




### የካርዱ ጀርባ




እያንዳንዱ የWellpoint DC ተመዝጋቢ የራሱ ወይም የራሷ ካርድ አላቸው። የተመዝጋቢ ID ካርድዎን ማንኛውም ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ በህግ የተከለከለ ነው።

| |
|---|
| **እባክዎ የተመዝጋቢ ID ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለበት ID ሁልጊዜ መያዝ ያስታውሱ። ማንኛውም የህክምና እንክብካቤ ከማግኘትዎ በፊት ወይም ከመድሃኒት ቤት መድሃኒት ከመውሰድዎ በፊት ሁልጊዜ ካርድዎን ያሳዩ።** |

## <u>የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)</u>

እርስዎ አሁን የWellpoint DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎ PCP (ዋና የሕክምና አቅራቢ) እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎ PCP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። እርስዎ Wellpoint DC ጋር ከመመዝገብዎ በፊት PCP ከነበሮት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**። ከፈለጉ ከዚያ PCP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

### የእርስዎን PCP ይምረጡ

1. እርስዎ Wellpoint DC ጋር ሲመዘገቡ PCP ይምረጡ። ይህ ሰው የWellpoint DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎ PCP ይሆናሉ።
    - የእርስዎ የአሁን PCP የWellpoint DC መረብ (ኔትዎርክ) አቅራቢ ከሆኑ፣ እዚያ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
    - እርስዎ PCP ከሌለዎት፣ ከኛ የአቅራቢ ማውጫ ካለው ዝርዝር ወይም **wellpoint.com/dc/medicaid** ጋር መምረጥ ይችላሉ።
    - ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለገዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።
    - በእኛ እቅድ ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥ PCP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PCP ካልወደዷቸው፣ የእርስዎን PCP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PCP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።
    - Wellpoint DC የተመዝጋቢ ID ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ የእርስዎን የPCP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።

2. የልጆችዎን ጨምሮ በእኛ እቅድ ውስጥ ያሉ የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ ቤተሰብ PCP ይምረጡ። የእርስዎ PCP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
    - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሙሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
    - የውስጥ ደዌ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ አዋቂ እና እድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆችን ብቻ ያክማሉ።
    - የሕጻናት ሐኪም - አዲስ ከተወለዱ ህጻናት ጀምሮ እስከ አዋቂ ያክማሉ
    - አዋላጅ ሐኪም/የማህጸን ሐኪም (OB/GYN) - የሴቶች ጤና እና የወሊድ ሕክምና ላይ ያተኮረ ነው።
    - እርስዎ ወይም ልጅዎ ልዩ የጤና ሕክምና የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ፣ ስፔሺያሊስትን እንደ PCP መምረጥ ይችላሉ።
3. የእርስዎን PCP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተሉትን ያድርጉ፦
    - ወደሚፈልጉት ሆስፒታል ሊልክዎ የሚችሉ ሐኪም ለመምረጥ ይሞክሩ። ሁሉም ሐኪሞች ታካሚዎችን ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድ PCP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
    - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡት PCP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። ሌላ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።
    - ለቤትዎ ወይም ለሥራዎ አቅራቢያ የሆነ ሐኪም ይምረጡ።

**የእርስዎን PCP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ**

የእርስዎን PCP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስ PCP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስ PCP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። አዲስ PCP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ።

**<u>የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)</u>**

እርስዎ አሁን የWellpoint DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎ PDP (ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ) እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎ PDP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። እርስዎ Wellpoint DC ጋር ከመመዝገብዎ በፊት የጥርስ ሐኪም ከነበሮት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**። ከፈለጉ ከዚያ PDP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

**የእርስዎን PDP መምረጥ**

1. እርስዎ Wellpoint DC ጋር ሲመዘገቡ PDP ይምረጡ። ይህ ሰው የWellpoint DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎ PDP ይሆናሉ።
   - የእርስዎ የአሁን PDP የWellpoint DC አውታረ-መረብ(ኔትዎርክ) አቅራቢ ከሆኑ፣ ከዚያ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
   - እርስዎ PDP ከሌለዎት፣ በአቅራቢ ማውጫችን ውስጥ ካለው የጥርስ ሐኪሞች ዝርዝር ወይም በ **wellpoint.com/dc/medicaid** መምረጥ ይችላሉ።
   - የጥርስ ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለገዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።
   - በእኛ እቅድ ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥ PDP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ የጥርስ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PDP ካልወደዷቸው፣ የእርስዎን PDP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎን PDP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።
   - Wellpoint DC የተመዝጋቢ ID ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ ላይ የእርስዎን የ PDP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።
   - የልጆችዎን ጨምሮ በእኛ እቅድ ውስጥ ለተመዘገቡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ PDP ይምረጡ። የእርስዎ PDP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
     - የቤተሰብ እና አጠቃላይ የጥርስ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሁሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
2. የእርስዎን PDP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተለውን ያስተውሉ፡-
   - የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድ PDP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
   - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡት PDP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። ሌላ የጥርስ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

**የእርስዎን PDP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ**

የእርስዎን PDP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስ PDP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስ PDP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። አዲስ PDP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ።

**<u>መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና</u>**

ሶስት (3) ዓይነት የጤና ሕክምና ሊስያስፈልጎት ይችላል፥ መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ ወይም ድንገተኛ ህክምና

**መደበኛ ህክምና**

መደበኛ ሕክምና ማለት ከእርስዎ PCP የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና ማለት ነው። መደበኛ ሕክምና የእርስዎ PCP ከላከዎት ሌሎች ሐኪሞች የሚያገኙት ሕክምናንም ይጨምራል። መደበኛ ሕክምና የክትትል ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ምርመራ፣ እና የስኳር፣ የደምግፊት፣ እና አስም የመሳሰሉ የጤና ችግሮች ሕክምና ሊሆን። መደበኛ ሕክምና ካስፈለጎት፣ የእርስዎ የPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ቀጠሮ ለመያዝ ይጠይቁ።

**አስቸኳይ ህክምና**

አስቸኳይ ሕክምና ማለት ወዲያውኑ ሳይሆን በ24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። አንዳንድ አስቸኳይ የሕክምና ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፥

- ማስታወክ
- ራስ ምታት
- ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን ከመጠን በላይ መጠቀም
- አነስተኛ ቃጠሎ ወይም ጥቃቅን ቁስል
- የጉሮሮ ህመም
- የባህሪይ ጤና
- የጆሮ ህመም
- የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር
- ከ101 ዲግሪ ፋራናይት በላይ ትኩሳት

**አስቸኳይ ሕክምና የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ የእርስዎ የPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ።**የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የስልክ ጥሪ የሚቀበለው ሰው ጋር መልእክት ያስቀምጡ። የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) ላይ ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ይነግርዎታል። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

**የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና**

ድንገተኛ ሕክምና ማለት ለከባድ እና ድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ የሆነ) ጉዳት ወይም በሽታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። ለድንገተኛ ሕክምና ማንኛውንም ሆስፒታል የመጠቀም መብት አሎት። ለድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች **ቅ**ድመ ፈቃድ አያስፈልግም።

- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ሕመም
- ራስን መሳት
- የማይቆም በጣም ከባድ የደም መፍሰስ
- በጣም ከባድ ቃጠሎ
- ኮንቨልዥን ወይም ሲዠር ተብሎ የሚጠራ መንቀጥቀጥ
- እየተባባሰ የሚሄድህ ህመም

**ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥምዎ ምን ማድረግ እንደሚችሉ**

1. **ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል (ER) ይሂዱ**
2. **ለER የWellpoint DC የተመዝጋቢ ID ካርድዎን ያሳዩ።**
3. **በተቻልዎ ፍጥነት፣ የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ።**

**<u>ከከተማ ውጭ ሲሆኑ የሚሰጥ እንክብካቤ</u>**

**ከከተማ ውጭ ሲሆኑ**

ከከተማ ውጭ ሆነው በሐኪም መታየት ወይም መድሃኒት መውሰድ ካስፈለጎት፣

**መደበኛ ህክምና**
ከከተማ ውጪ ሐኪም ጋር ወይም ሌላ አቅራቢ ጋር ሲሄዱ ለሐኪም የምንከፍልልዎ መሆን አለመሆኑን ወደኛ ደውለው መጠየቅ አለብዎ ምክንያቱም በColumbia ዲስትሪክት ውስጥ ያልሆኑ ሐኪሞች የWellpoint DC አካል አይደሉም። ሕክምናውን ከማግኘትዎ በፊት Wellpoint DC እንደሚቻል ካልነገሮት፣ የሚከፍሉት እርስዎ እራስዎ ኖት። ከከተማ ውጭ ሆነው ከሐኪም መድሃኒት ካስፈለግዎ፣ የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። እርዳታ ከፈለጉ፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

**አስቸኳይ ህክምና**
የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) ላይ በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ሊነግርዎ ይችላሉ። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

**የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና**

የአእምሮ ጤና፣ የአልኮል፣ ወይም ሌላ የአደንዛዥ እጽ ድንገተኛ አደጋን ጨምሮ ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመዎት፣ ወዲያውኑ ህክምና ለማግኘት አቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ህክምና ክፍል (ER) ይሂዱ። ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ከገቡ፣ የER ሰራተኞች ወደ እርስዎ PCP እንዲደውሉ መጠየቅ አለብዎ። ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ከገቡ፣ በተቻለ ፍጥነት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይኖርብዎታል። **ለድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች ቅድመ ፈቃድ አያስፈልግም።**

**ከአውታረ-መረብ ውስጥ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች**

Wellpoint DC ወደ አንዱ ሐኪሞችን ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር ሲሄዱ ለእርስዎ ሕክምና ይከፍላል። እኛ እነዚህን ሐኪሞች እና ሌሎች የጤና ሕክምና አቅራቢዎች የእኛ "መረብ" አቅራቢዎች ብለን እንጠራቸዋለን። የእኛ ያልሆነ ሐኪም ወይም አቅራቢ "ከመረብ ውጪ" አቅራቢ ተብሎ ይጠራል። እነዚህ ሁሉም "የመረብ ውስጥ" ሐኪሞች በአቅራቢ ማውጫዎ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

"ከአውታረ-መረብ ውጪ" የሆነ ሐኪም፣ ሆስፒታል፣ ወይም ላብራቶሪ ጋር ከሄዱ፣ ለሕክምናዎ መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል። መጀመሪያ እኛን ቢጠይቁን እና እኛ እንደሚቻል፣ አብዛኛውን ጊዜ በጽሁፍ፣ ነግሮኖት ቢሆን ኖሮ፣ መክፈል አይኖርብዎትም ነበር። እኛ ይህን "ቅድመ ፈቃድ" ብለን እንጠራዋለን።

Wellpoint DC ሽፋን ያለውን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የመረብ ውስጥ አቅራቢ ከሌለው Wellpoint DC አስቀድሞ ከጸደቀ ከመረብ ውጪ ከሆነ አቅራቢ ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶች ይሰጣል (በቂ እና በትክክለኛ ጊዜ)።

**ቅድመ ፈቃድ (PA)** ማለት በመደበኛነት በWellpoint DC ሽፋን ላልተሰጠው የጤና አገልግሎት ፈቃድ ማለት ነው። አገልግሎቱን ከማግኘትዎ በፊት ይህን ፈቃድ ማግኘት አለብዎ። ድንገተኛ ሕክምና ለማግኘት PA አያስፈልግዎትም። PA ስለ ማግኘት ለመጠየቅ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

ከመረብ ውጪ ቢሆኑም፣ የመረጡት የቤተሰብ ምጣኔ አቅራቢ ጋር መሄድ ይችላሉ። የቀደመ ፈቃድ አያስፈልግም። ገጽ 21 ይመልከቱ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት።

## ቀጠሮ ማስያዝ

### የእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ

- የተመዝጋቢ ID ካርድዎን እና እርሳስ እና ወረቀት አጠገብዎ ያድርጉ።
- የእርስዎ PCP ቢሮ ጋር ይደውሉ። በተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎ ፊት ገጽ ላይ የእርስዎን PCP የስልክ ቁጥር ይፈልጉ። በተጨማሪም በእርስዎ የአቅራቢ ማውጫ ወይም አንላይን በ**wellpoint.com/dc/medicaid** ሊያገኙት ይችላሉ።
- ስልኩን ለሚያነሱት ግለሰብ እርስዎ የWellpoint DC ተመዝጋቢ እንደሆኑ ይንገሯቸው። የእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ መያዝ እንደፈለጉ ይንገሯቸው።
- ቀጠሮ መያዝ ለምን እንዳስፈለግዎት ለግለሰቡ ይንገሯቸው። ለምሳሌ፥
  - እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ ተመዝጋቢ ሕመም እየተሰማችሁ ነው
  - እራስዎን ጎድተዋል ወይም አደጋ አጋጥምዎታል
  - ምርመራ ወይም የክትትል ምርመራ ያስፈልግዎታል
- የቀጠሮዎን ጊዜ እና ቀን ይጻፉት።
- በቀጠሮዎ ቀን በሰዓቱ ይገኙ እና የተመዝጋቢ ID ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለው መታወቂያ ይያዙ።
- ቀጠሮ ለማስያዝ እርዳታ ካስፈለገዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

### ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ

- በቀጠሮዎ መገኘት እና በሰዓቱ መምጣት በጣም አስፈላጊ ነው።
- ቀጠሮዎን መቀየር ወይም መሰረዝ ካለብዎ፣ እባክዎ ከቀጠሮዎ 24 ሰዓታት በፊት ወደ ሐኪምዎ ይደውሉ።
- ለአንዳንድ ቀጠሮዎች፣ ቀጠሮውን ለመሰረዝ ከ 24 ሰዓታት የበለጠ ቀደም ብለው መደወል ሊኖርብዎ ይችላል።
- በቀጠሮዎ ላይ ካልተገኙ፣ ወይም ከዘገዩ፣ ሐኪምዎ ታካሚያቸው እንደማይሆኑ ሊወስኑ ይችላሉ።

### የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት

ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የእርስዎን PCP ወይም PDP ማናገር ካስፈለግዎ፣ የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ስልኩን የሚያነሱት ግለሰብ ጋር መልእክትዎን እና ስልክ ቁጥርዎን ያስቀምጡ። በተቻለ ፍጥነት አንድ ሰው ይደውልልዎታል። ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመዎት፣ ወደ 911 ይደውሉ ወይም የድንገተኛ ሕክምና ክፍል ይሂዱ። እንዲሁም፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) ላይ በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

### ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?

የሐኪምዎ ቢሮ በደወሉ በጥቂት ቀናት ውስጥ ለእርስዎ ቀጠሮ መስጠት ይኖርበታል። በእነዚህ ጊዜያት ቀጠሮ ማግኘት ካልቻሉ እባክዎ ወደ **833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። ከታች ያለው ሰንጠረዥ ቀጠሮ ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ እንደሚፈጅ ያሳያል።

| የጉብኝት ዓይነት | የእርስዎ ሁኔታ | ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? |
|---|---|---|
| **አስቸኳይ ጉብኝት** | ተጎድተዋል ወይም ታመዋል እና እንዳይብስብዎ በ24 ሰዓታት ውስጥ ሕክምና ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አሁኑኑ ሐኪም ማየት አያስፈልግዎትም።<br>አንዳንድ ምሳሌዎች አነስተኛ ቃጠሎዎች፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ ህመም፣ ወይም የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር ናቸው። | በ 24 ሰዓታት ውስጥ |
| **መደበኛ ጉብኝት** | አነስተኛ ህመም ወይም ጉዳት አለብዎ ወይም መደበኛ ምርመራ ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አስቸኳይ ቀጠሮ አያስፈልግዎትም። | በ 30 ቀናት ውስጥ |
| **የክትትል ጉብኝት** | ከህክምናው በኋላ ዶክተርዎን ማየት ያስፈልግዎታል። በደንብ እየተሻለዎት መሆኑን ብቻ ማረጋገጥ አለብዎት። | ከ 1-2 ሳምንታት ውስጥ፣ እንደ ሕክምናው ዓይነት |
| **የአዋቂ የጤንነት ምርመራ ጉብኝት** | • አዲስ ሐኪም ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎን እየያዙ ነው<br>• መደበኛ የአዋቂ ምርመራዎ ደርሷል<br>• የፕሮስቴት ምርመራ፣ የፔልቪክ ምርመራ፣ የ PAP ስሚር፣ ወይም የጡት ምርመራዎ ደርሷል። | በ 30 ቀናት ውስጥ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከዚያ በፊት |
| **ስፔሺያሊስቶች ጋር አስቸኳይ ያልሆኑ ቀጠሮዎች (በሪፈራል)** | የእርስዎ PCP አስቸኳይ ላልሆነ ሁኔታዎ ስፔሺያሊስት እንዲያዩ ሪፈር አድርገዎታል። | በ 30 ቀናት ውስጥ |
| **የልጅ EPSDT ምርመራዎች - አስቸኳይ ያልሆነ** | ልጅዎ ለቅድመ እና ወቅታዊ የፍተሻ፣ የምርመራ እና ህክምና (EPSDT) ፍተሻ ሊቀርብ ነው። | የመጀመሪያ ምርመራ፥<br>በ 60 ቀናት ውስጥ<br><br>ተጨማሪ ምርመራዎች ፥<br>እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ከቀጠሮ ቀን በ 30 ቀናት ውስጥ፤<br>እድሜያቸው ሁለት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆች ከቀጠሮ ቀን በ 60 ቀናት ውስጥ |
| **IDEA (የቀደመ ጣልቃገብነት) ግምገማዎች** | ምርመራዎች ("ግምገማዎች") እድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ የእድገት መዘግየት ወይም ጉድለት ስጋት ላለባቸው ልጆች | በ 30 ቀናት ውስጥ |

## <u>የድጋፍ አገልግሎቶች</u>

### የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/መስማት እና ማየት ለተሳናቸው ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች

### የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

Wellpoint DC በሆስፒታሉ ውስጥ ጨምሮ የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን በነጻ ይሰጣል።

እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ ለአስተርጓሚ አገልግሎቶች። የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ከሐኪም ቀጠሮዎ በፊት ይደውሉልን።

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት በስልክ ነው። የሐኪም ቀጠሮዎ ላይ አስተርጓሚ ከእርስዎ ጋር እንዲገኙ ካስፈለጎት፣ በ 48 ሰዓታት ወይም በ 3-5 ቀናት ውስጥ ውስጥ ለኛ ማሳወቅ አለብዎ። በአካል ፊት ለፊት የትርጉም አገልግሎትን የሚያስፈልግ ልዩ ሁኔታ ካለ፣ ተመዝጋቢዎቹ ወይም አቅራቢዎቹ ከWellpoint DC የቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። ተመዝጋቢዎች ወይም አቅራቢዎች የፈቃድ ጥያቄን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለማስገባት የኛን የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ቡድንን ማነጋገር ይችላሉ።

**የትርጉም አገልግሎቶች**

ከWellpoint DC መረጃ ካገኙ እና ወደ ሌላ ቋንቋ እንዲተረጎምልዎ ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

**መስማት እና ማየት ለተሳናቸው ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች**

የመስማት ችግር ካለብዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ711።

የማየት ችግር ካለብዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ። እኛ ለእርስዎ መረጃ በኦዲዮ ቴፕ በብሬል ወይም በትልቅ እትመት ልንሰጦት እንችላለን።

## <u>የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራሎች</u>

**የስፔሺያሊቲ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል**

የእርስዎ ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ (PCP) አብዛኛውን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ ይችላል፣ ነገር ግን ከሌላ የአቅራቢዎች አይነት እንክብካቤ ሊፈልጉ ይችላሉ። እኛ ለህክምና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች እንክብካቤዎችን ከሚሰጡ ከተለያዩ አይነት አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት እንሰጣለን። እነዚህ አቅራቢዎች በልዩ የሕክምና መስክ ልዩ ስልጠና ስለወሰዱ ስፔሻሊስቶች ተብለው ይጠራሉ።

የስፔሻሊስቶች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፥

- አለርጂስትስ (የአለርጂ እና የአስም ሐኪሞች)
- ዴርማቶሎጂስት (የቆዳ ሐኪሞች)
- ካርዲዮሎጂስት (የልብ ሐኪሞች)
- ኢንዶክሪኖሎጂስት (የስኳር በሽታ እና የታይሮይድ ሐኪሞች)
- ፖዲያትሪስቶች (የእግር ሐኪሞች)
- ኦንኮሎጂስት (የካንሰር ሐኪሞች)
- ኦብስቴትሪክስ/ጋይናኮሎጂ (የጽንስና የማህፀን ሕክምና) (OB/GYN)

ስፔሺያሊስት ማየት ከፈለጉ፣ ነገር ግን Wellpoint DC ለሕክምናው እንደማይከፍል ከነገሮት፣ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፥

- በWellpoint DC መረብ ውስጥ ያለ ሌላ ሐኪም ጋር ቀጠሮ በማስያዝ ሁለተኛ አስተያየት ያግኙ
- በውሳኔያችን ላይ ይግባኝ ያቅርቡ (በይግባኝ ላይ ገጽ 45 ይመልከቱ)
- ፍትሃዊ ችሎት ይጠይቁ (ስለ ፍትሃዊ ችሎቶች ገጽ 45 ይመልከቱ)

**የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች**

ከእርስዎ PCP የቀደመ ፈቃድ ሳያስፈልግዎ ማግኘት የሚችሏቸው የተወሰኑ አገልግሎቶች አሉ። እነዚህ የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች ተብለው ይጠራሉ እና ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

**ለሚከተሉት ሪፈራል አያስፈልግዎትም፥**

- የእርስዎን PCP ለማየት
- ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥምዎ ሕክምና ለማግኘት
- ለመደበኛ ወይም የመከላከል አገልግሎቶች በመረብዎ ውስጥ ያሉ የእርስዎ የአዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም (OB/GYN) አገልግሎቶች ለማግኘት (ለሴቶች ብቻ)
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች (STI) አገልግሎቶች ለማግኘት
- ክትባቶች (መርፌዎች) ለማግኘት
- በመረብ ውስጥ የሚገኝ የዓይን ሕክምና አቅራቢ ጋር ለመሄድ
- ልጅዎን በመረብ ውስጥ የሚገኝ የጥርስ ሕክምና አቅራቢ ጋር ለመውሰድ
- ከአልኮል ወይም ከሌሎች መድኃኒቶች ጋር ለተያያዙ ችግሮች የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ይቀበሉ

**የባህሪ ጤና (የአእምሮ ጤና ወይም የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መታወክ አገልግሎቶች)**

የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት የእርስዎን PCP ማየት **አያስፈልግዎትም**። ነገር ግን፣ በእኛ አውታረ መረብ ውስጥ ካለ ሰው የእርስዎን እንክብካቤ ማግኘት ያስፈልግዎታል። አሁን እንክብካቤ እያገኙ ከሆነ፣ አቅራቢዎን **Wellpoint DC**ን እንደሚወስዱ ይጠይቁ።
ከመጀመሪያው ጉብኝትዎ በፊት፡-

1. **የቀድሞ** ዶክተርዎ መዝገቦችዎን ወደ አዲሱ አገልግሎት ሰጪዎ እንዲልክ ይጠይቁት። ይህ ምንም አያስከፍልዎትም። አገልግሎት ሰጪዎ ስለ ፍላጎቶችዎ እንዲያውቅ ይረዳሉ።
2. **ከአዲሱ አገልግሎት አቅራቢዎ ጋር** ቀጠሮ ለመያዝ ሲደውሉ የ**Wellpoint DC** ካርድዎን ያዘጋጁ።
3. የ**Wellpoint DC** ተመዝጋቢ መሆንዎን ይናገሩ እና የእርስዎን **Medicaid ID ቁጥር** ይስጡ።
4. የቀጠሮዎን ቀን እና ሰዓት ይፃፉ። አዲስ ታካሚ ከሆኑ፣ አቅራቢው ቶሎ እንዲመጡ ሊጠይቅዎት ይችላል። እዚያ እንድገኙ የጠየቁዎትን ጊዜ **ይጻፉ**።
5. አገልግሎት ሰጪዎን ለመጠየቅ የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች **ዝርዝር ያዘጋጁ**። ያጋጠሙዎትን ማንኛውም ችግሮች ይዘርዝሩ።

**በቀጠሮው ቀን፥**

1. **አገልግሎት** ሰጪዎ እንዴት እንደሚረዳዎት እንዲያውቅ ሁሉንም መድሃኒቶችዎን እና የጥያቄዎችን ዝርዝር ከእርስዎ ጋር **ይዘው ይሂዱ**።
2. **ለጉብኝትዎ** በሰዓት ይገኙ። ቀጠሮዎን ማክበር ካልቻሉ፣ እባክዎ አዲስ ጊዜ ለማግኘት ለአገልግሎት ሰጪዎ ይደውሉ።
3. **የWellpoint DC ID ካርድዎን ከእርስዎ** ጋር ይዘው ይሂዱ። አገልግሎት አቅራቢዎ ቅጂ ሊያደርግ ይችላል።

በመደወል የባህሪ ጤና እና የቁስ አጠቃቀም መታወክ እርዳታ ወዲያውኑ ማግኘት ይችላሉ **833-359-1384 (TTY 711)**። ለእርስዎ/ልጅዎ ምርጡን አቅራቢ እንዲያገኙ እንረዳዎታለን። 24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት መደወል ይችላሉ።

**9-1-1** ላይ መደወል አለብዎት፣ እርስዎ/ልጅዎ ለሕይወት አስጊ የሆነ የባህሪ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ እያጋጠማችሁ ከሆነ። እንዲሁም ወደ ቀውስ ማእከል ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል መሄድ ይችላሉ። እርዳታ ለማግኘት ድንገተኛ ሁኔታ መጠበቅ አያስፈልግዎትም።

ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆነ፣ ለ**Wellpoint DC የአስተርጓሚ አገልግሎት የስልክ መስመር መደወል ይችላሉ።** መስማት የተሳነዎት ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት፣ በ**711** ወደ TTY መስመራችን ይደውሉ።

እንዲሁም በ**988** መደወል ይችላሉ። የ988 ራስ ማጥፋት እና ቀውስ የህይወት-መስመር ራስን የማጥፋት ወይም ከባህሪ ጤና ጋር በተዛመደ ጭንቀት ውስጥ ላሉ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም ስጋቶች ላሉባቸው ሰዎች የ 24/7 ሚስጥራዊ ድጋፍ ይሰጣል።

- የሞባይል ቀውስ አገልግሎቶች (ልጆች/ወጣቶች) CHAMPS በ202-481-1440 - በሳምንቱ ውስጥ የባህሪ ወይም የአዕምሮ ጤና ችግር ለሚገጥማቸው ልጆች፣ በቤት፣ በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ ውስጥ የሞባይል በቦታው ላይ የድንገተኛ እርዳታ ይሰጣል። አገልግሎቶቹ ከ6-21 አመት ለሆኑ ህጻናት እና ወጣቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ቅዳሜና እሁድ፣ እባክዎ ለማህበረሰብ ምላሽ ቡድን ይደውሉ።
- የቅድመ ልጅነት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች (Healthy Futures) በ202-698-1871 - ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ህጻናት የችግር ጣልቃገብነት እና የድጋፍ ማእከል ሰራተኞች በግለሰብ የልጆች ባህሪ እና የክፍል አስተዳደር ላይ ያቀርባል።

**የአልኮል መጠጥ ወይም ሌሎች የአደንዛዥ እጽ ችግር አገልግሎቶች**

የአልኮል መጠጥ ወይም ሌላ የአደንዛዥ እጽ ችግሮች ለጤናዎ አደገኛ ነው እና አቅራቢያዎ ላሉ ሰዎች ጤናም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ለእነዚህ ችግሮች እርዳታ ካስፈለጎት ወደ ሐኪም መሄድ አስፈላጊ ነው። Wellpoint DC የዲቶክስፊኬሽን (የጸረ መርዛማነት) አገልግሎቶችን በማመቻቸት ይረዳዎታል እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያግዝዎትን የእንክባካቤ ቅንጅትን ያቀርብልዎታል። ለእነዚህ ችግሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- የWellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)**፣ 24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት ይደውሉ።
- የግምገማ እና ሪፈራል ማእከል (ARC) በቀጥታ በ202-727-8473 ወይም 75 Florida Ave. NE, Washington, DC 20002. በመነብኘት ያግኙ። ARC የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መታወክ ህክምና ለሚፈልጉ ግለሰቦች የተመሳሳይ ቀን ግምገማ እና ሪፈራል ያቀርባል፣ ይህም መመረዝን መቆጣጠር፣ በመድሃኒት የታገዘ ህክምና እና የግለሰብ እና የቡድን ምክርን ይጨምራል።
- የDC ማረጋጊያ ማእከልን በ202-839-3500 ወይም 35 K St. NE Washington, DC 20001 በመጎብኘት ያግኙ። የDC ማረጋጊያ ማዕከል በአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም ቀውስ ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚፈልጉትን እርዳታ ለማግኘት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይሰጣል፣ እና የተፈቀደላቸው መድኃኒቶችን በቦታው ይሰጣል፣ ማማከር እና ሪፈራል እና የረጅም ጊዜ የሕክምና አማራጮች ውስጥ መመደብን ይሰጣል። 24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት ክፍት ነው።

ሁሉም የባህሪይ ጤና፣ የአልኮል መጠጥ፣ እና የአደንዛዥ እጽ ሱስ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

**የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች**

የወሊድ መቆጣጠሪያ ወይም ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ሁሉም የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ከመረጡት ማንኛውም አቅራቢ ማግኘት ይችላሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ከእርስዎ PCP ውጪ ሌላ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሐኪም ከመረጡ፣ ለእርስዎ PCP ይንገሯቸው። የእርስዎ PCP ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል። ከእርስዎ PCP ጋር ይነጋገሩ ወይም ወደ Wellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ፣ ለወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ።

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታል፥**

- የእርግዝና ምርመራ
- ለሴቶች እና ለጥንዶቹ የምክር አገልግሎት
- መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ

- የምክር አገልግሎት እና ክትባቶች
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ሕክምና
- የማምከን ሕክምና (21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን ያስፈልጋል እና ከሕክምናው 30 ቀናት በፊት ቅጹን መፈረም ይጠይቃል)
- የHIV/AID ምርመራ እና የምክር አገልግሎት

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን አያካትቱም፥**

- መደበኛ የመሃንነት ምርመራዎች ወይም ሕክምናዎች
- ለማምከን ማህጸንን ማውጣት
- በፈቃደኝነት የተከናወነ መሃንነትን ለመለወጥ
- የኤችአይቪ/ኤድስ ሕክምና
- ማስወረድ

**የHIV/AIDS ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት፣ እና ሕክምና**

የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሲኖሮት
- ከራስዎ PCP
- ከHIV/AID ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማዕከል

የHIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት የት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**። የHIV/AID ሕክምና ካስፈለገዎት፣ የእርስዎ PCP ሕክምና እንዲያገኙ ያግዝዎታል። ወይም ለ**833-359-1384 (TTY 711)** መደወል ይችላሉ። በተጨማሪ ሐኪምዎ ለHIV/AIDS ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳለዎት ካመኑ፣ የቅድመ መጋለጥ ፕሮፊላክሲስ (PrEP) ማግኘት ይችላሉ።

**<u>የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች</u>**

መድሃኒት ቤቶች መድሃኒትዎን ማግኘት የሚችሉበት ቦታ ነው። ሐኪምዎ የመድሃኒት ማዘዣ ከሰጠዎት፣ በWellpoint DC መረብ ውስጥ ወዳለ መድሃኒት ቤት መሄድ አለብዎት።

በWellpoint DC አውታረ-መረብ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የመድሃኒት ቤቶች ዝርዝር በእርስዎ የአቅራቢ ማውጫ ወይም ኦንላይን በ **wellpoint.com/dc/medicaid** ማግኘት ይችላሉ።

ከከተማ ውጪ ከሆኑ፣ ድንገተኛ ሕክምና፣ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ካስፈለገዎት፣

- እየተጓዙ ከሆነ እና ለአረፍት ጊዜዎ የመድሃኒትዎን አቅርቦት ከፈለጉ፣ ወደ መድሃኒት ቤት(ፋርማሲ) ተመዝጋቢ አገልግሎት በ**833-214-3604 (TTY 711)** ይደውሉ። ለእረፍት ጊዜዎ ለ30 ቀን ድረስ የሚበቃ የመድሃኒት አቅርቦት ሊያገኙ ይችላሉ።
- ለድንገተኛ አገልግሎት፣ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ ወይም ወደ 911 ይደውሉ።
- ለአስቸኳይ ሕክምና፥
    - የእርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። የእርስዎ የPCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ ቁጥር ይተዉ። የእርስዎ PCP ወይም ተተኪው ባለሞያ መልሰው ይደውልልዎታል።

- o የእርስዎን PCP ምክር ያክብሩ። ሕክምናውን በምን ያህል ፍጥነት ማግኘት እንዳለብዎት እና ሕክምናውን የት እንደሚያገኙ ሊነገርዎት ይችላል።
- o እርዳታ ከፈለጉ፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine) ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

**የሐኪም ማዘዣዎን ለማስሞላት፥**

- የWellpoint DC መረብ አካል የሆነ እና ለሥራዎ ወይም ለቤትዎ ቅርብ የሆነ መድሃኒት ቤት ይምረጡ።
- የሐኪም ማዘዣ ካሎት፣ ወደ መድሃኒት ቤቱ ይሂዱ እና ለፋርማሲስቱ የሐኪም ማዘዣዎን እና የእርስዎን የWellpoint DC የተመዘገቢ ID ካርድ ይስጧቸው።
- እርዳታ ካስፈለገዎት፣ እባክዎ ወደ የመድሃኒት ቤት የተመዘጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-214-3604 (TTY 711)** ይደውሉ።

**ማስታወስ የሚያስፈልጉ ነገሮች፥**

- ለመድሃኒቶችዎ እንዲከፍሉ መጠየቅ የለብዎትም። መድሃኒት ቤቱ ወይም የመድሃኒት መደብሩ እንዲከፍሉ ከጠየቅዎ የWellpoint DC የተመዘጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ ሐኪምዎ ለመድሃኒት ከWellpoint DC የቀደመ ፈቃድ (PA) ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ሐኪምዎ የቀደመ ፈቃዱን(PA) ለማግኘት በሚጠባበቁበት ጊዜ፣ እርስዎ መድሃኒቱን የማግኘት መብት አሎት፥
  - o እስከ 72 ሰዓታት ወይም
  - o ወይም የመድሃኒቱን አንድ ሙሉ ዙር በቀን ከአንድ ጊዜ ያነሰ የሚወስዱት ከሆነ

<u>**መድሃኒትዎን ካልተቀበሉ፥**</u>

- ዛሬ መድሀኒትዎን እንዳያገኙ የሚከለክልዎ ጉዳይ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ለሶስት ቀናት የሚቆይ የመድሃኒት አቅርቦትን ከፋርማሲስትዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- በሐኪም የታዘዙትን መድሃኒቶች እና ምክንያቱን መቀበል ካልቻሉ ፋርማሲዎ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጣል።
- አስተዳደራዊ ፍትሃዊ ችሎት ከመጠየቅዎ በፊት የሚተዳደረው የእንክብካቤ እቅድዎ የሚያቀርባቸውን ሁሉንም የውድቅ ማድረጊያ ሂደቶች ማጠናቀቅ አለብዎት።
- የመድሃኒት ጥያቄዎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ውድቅ የተደረገ ወይም የተቀነሰ ከመሰለዎት የአስተዳደር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። ፍትሃዊ ችሎት ለመጠየቅ:-
  - ለDHCF እንባ ጠባቂ በ202-724-7491 ይደውሉ ወይም ወደ healthcareombudsman@dc.gov ኢሜይል ይላኩ
  - ወደ አስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ ይደውሉ በ202-442-9094
  - ወይም 441 4th Street, NW, Suite 450 North, Washington, DC 20001 ይጎብኙ።

<u>**በሽታ መቆጣጠር**</u>

እርስዎ ከባድ በሽታ ካለብዎ ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጎት፣ የኛ የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም ውስጥ ልናስገባዎ እንችላለን። ይህ ማለት የበሽታ ተቆጣጣሪ ይኖርዎታል ማለት ነው። የበሽታ ተቆጣጣሪ የሚሰራው ለWellpoint DC ነው እና በሽታዎን ለመቆጣጠር እና ጤናማ ለመሆን የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶች እና መረጃ እንዲያገኙ ያግዝዎታል።

## የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች

እርስዎ ወይም ልጅዎ ከባድ በሽታ ካለባችሁ ወይም ለስኳር በሽታ፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የአእምሮ በሽታ፣ ወይም አስም ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጋችሁ፥ Wellpoint DC የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን የሚያግዙ ልዩ አገልግሎቶችን እና ፕሮግራሞችን ሊያቀርብልዎ ይችል ይሆናል። እርስዎ ወይም ልጅዎ በሽታችሁን ለመቆጣጠር እና ጤናችሁን ለማሻሻል የሚያስፈልጋችሁን አገልግሎቶችን እና መረጃ እንድታገኙ ለማስቻል የጤና ሕክምና አስተዳዳሪ ይኖርዎታል።

የWellpoint DC የጤና ሕክምና አስተዳዳሪ ለእርስዎ እና ለልጅዎ በሚከተሉት ላይ ያግዝዎታል፥

- የእርስዎን የተሸፈኑ አገልግሎቶች ማግኘት እና መረዳት፤
- የሕክምና ቀጠሮዎች እና ምርመራዎችን ማዘጋጀት፤
- ትራንስፖርት ማዘጋጀት፤
- ትክክለኛውን አገልግሎት ማግኘትዎን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መፈለግ፤
- ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶችዎን ለማገዝ ግብዓቶችን መፈለግ እና/ወይም ሕክምና ሰጪዎች የእለትተለት ውጥረቶቻቸውን እንዲቆጣጠሩ የሚያስችል እገዛ መስጠት፤
- የማህበረሰብ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት፤ እና
- ጥቅማጥቅሞችዎ ሲያበቁ፣ ወደ ሌላ ሕክምና ለመሸጋገር፣ ሌላ MCP ሲመርጡ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ወደ ሌላ የDC Medicaid ፕሮግራም ሲቀየሩ

የእኛ ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላሉ። እነሱ በተጨማሪ በአሁን ወቅት ለየትኞቹ ፕሮግራሞች እርስዎ እንደተመዘገቡ ሊያሳውቅዎ ይችላሉ። በተጨማሪም ሪፈራል ወይም ከአንድ ፕሮግራም ለመውጣት መጠየቅ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ Wellpoint DC የህክምና አስተዳደር ፕሮግራምን በ**833-346-1663** ያነጋግሩ።

## አዋቂ ሰዎችን ከመታመም የሚከላከሉ አገልግሎቶች

Wellpoint DC ጤናዎን እንዲጠብቁ ይፈልጋል። እኛ በተጨማሪ የኛ የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች ጋር እንዲመዘገቡ እንፈልጋለን። የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች የማጣሪያ ምርመራዎችን፣ የምክር አገልግሎት እና ክትባቶችን ያካትታሉ።

### የክትትል ምርመራዎች ምክረሀሳቦች ("ማጣሪያዎች")

እባክዎ ቀጠሮ ይያዙ እና ለክትትል ምርመራ በየአመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ የእርስዎ PCP ጋ ይሂዱ። በክትትል ምርመራዎ ወቅት ከእርስዎ PCP ጋር ሊያወሯቸው ስለሚችሉ ነገሮች በ "የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች" ክፍል ላይ "የአዋቂ የደህንነት አገልግሎቶች" ዝርዝርን ይመልከቱ።

### የመከላከል የምክር አገልግሎት

የመከላከል የምክር አገልግሎት ለእርስዎ የሚቀርበው እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ለማስቻል ነው። በሚከተሉት ነገሮች ላይ የመከላከል የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- ምግብ እና የአካል እንቅስቃሴ
- የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም
- ሲጋራ ማጨስ ማቆም
- የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል
- የእርግዝና መከላከያ ሕክምና

## የአዋቂ ክትባቶች

አዋቂ ከሆኑ የተወሰነ ክትባቶች (መርፌዎች) ሊያስፈልግዎ ይችላል። የትኞቹ እንደሚያስፈልግዎ ለማወቅ እባክዎ የእርስዎ PCP ጋር ያውሩ።

## <u>እርግዝና</u>

እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ የአዋላጅ ሐኪምዎ/የማህጸን ሐኪምዎ ጋር ወዲያውኑ መሄድ አስፈላጊ ነው። ይህን ቀጠሮ ከመያዝዎ በፊት የእርስዎን PCP ማየት አያስፈልግዎትም።

**እርጉዝ ከሆኑ፣ እባክዎ ይደውሉ፥**

- የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) በ202-727-5355 እርግዝናዎን ሪፖርት ለማድረግ
- የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)**
- የእርስዎ PCP

እርጉዝ ከሆኑ ሊመረመሯቸው የሚገቡ የተወሰኑ ነገሮች አሉ። እነዚህ ጤናማ እርግዝና፣ ወሊድ፣ እና ህጻን እንዲኖርዎ ለማረጋገጥ ያግዛሉ። ይህ ቅድመ ወሊድ ሕክምና ተብሎ ይታወቃል። ህጻን ልጅዎ ከመወለዱ በፊት የቅድመ ወሊድ ሕክምና ያገኛሉ።

| |
|---|
| **ያስታውሱ፣ እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከጠረጠሩ፥**<br>**አልኮል አይጠጡ፣ አደንዛዥ ዕፅ አይጠቀሙ ወይም አያጨሱ።** |

## የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ ሕክምና

**ለነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች ልዩ እንክብካቤ**

Taking Care of Baby and Me® ለሁሉም ነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች የWellpoint DC ፕሮግራም ነው። ነፍሰ ጡር በሚሆኑበት ጊዜ የእርስዎን ዋና የእንክብካቤ አቅራቢዎን (PCP) ወይም የጽንስ እና የማህፀን ሐኪም (OB/GYN) ማየት በጣም አስፈላጊ ነው። አስቀድመው ልጅ የወለዱ ቢሆንም እንኳን የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። በፕሮግራማችን፣ ተመዝጋቢዎች የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ እንክብካቤ ለማግኘት መረጃ እና ሽልማቶችን ያገኛሉ።

በተጨማሪ የኛ ፕሮግራም የተወሳሰበ የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ነፍሰጡር ተመዝጋቢዎችንም ያግዛል። የነርስ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉትን ለማቅረብ ከእነዚህ ተመዝጋቢዎች ጋር በቅርበት ይሰራሉ፥

- ትምህርት
- ስሜታዊ ድጋፍ
- የሐኪሞቻቸውን የእንክብካቤ እቅድ እንዲተገብሩ ማገዝ
- እንደ ማጓጓዣ፣ የሴቶች ጨቅላ ህጻናት እና ልጆች (WIC)፣ የቤት ውስጥ የጉብኝት ፕሮግራሞች፣ የጡት ማጥባት ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት የመሳሰሉ በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች እና ግብአቶች መረጃ

በተጨማሪ ነርሶች ከሐኪሞች ጋር ይሰራሉ እና ተመዝጋቢዎች ሊፈልጓቸው በሚችሉ ሌሎች አገልግሎቶች ላይ እገዛ ያደርጋሉ። ግቡ ለተመዝጋቢዎች የተሻለ ጤናን እና ጤናማ ሕፃናትን እንዲወለዱ ማድረግ ነው።

**ልጅዎን ከወለዱ በኋላ፣ ለተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ833-359-1384 (TTY 711) እና ESA በ202-727-5355 ይደውሉ።**

**የልጅዎ ጤና**

**<u>የHealthCheck ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራም ለልጆች (EPSDT)</u>**

Wellpoint DC ልጆችዎ ጤናማ ሆነው እንዲያድጉ ይፈልጋል። ልጅዎ በDC Healthy Families (Medicaid) ፕሮግራም ውስጥ ካለ/ች፣ ልጅዎ የቀደመ እና በየጊዜው የሚደረግ የማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ሕክምና (EPSDT) ተብሎ በተጨማሪነት በሚታወቀው የHealthCheck ፕሮግራም ውስጥ ይኖራሉ። ይህ የሜዲኬይድ ፕሮግራም የህፃናት ህክምና ክፍል ሲሆን የሚጀምረው ልጅዎ ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ሲሆን ልጅዎ 21 አመት እስኪሞላው ድረስ ይቆያል። የHealthCheck ፕሮግራም ለልጅዎ ብዙ ጠቃሚ ምርመራዎችን ይሰጣል።

በዚህ የመምሪያ መጽሃፍ ውስጥ የHealthCheck (EPSDT) የመረጃ ወረቀት ይኖራል።

## የHealthCheck ፕሮግራም ለልጆች

ልጆችዎ ጤናማ ሆነው እንዲያድጉ ማገዝ እንፈልጋለን። ልጅዎ በDC ጤናማ ቤተሰቦች (DC Healthy Families) (Medicaid) ፕሮግራም ውስጥ ካለ/ች፣ ልጅዎ የቀደመ እና በየጊዜው የሚደረግ የማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ሕክምና (EPSDT) ተብሎ በተጨማሪነት በሚታወቀው የHealthCheck ፕሮግራም ውስጥ ይኖራሉ። መደበኛ ምርመራ ማድረግ የጤና ችግሮችን ቶሎ ለመለየት ይረዳል፣ እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የጤና ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል ይረዳል።

በHealthCheck፣ ልጅዎ ከተወለደ/ች ጀምሮ እስከ 21 አመት ድረስ ምንም አይነት የወጪ የሌላቸው ምርመራዎችን ያገኛሉ፣ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፦

- ሙሉ የአካል ምርመራ
- የእድገት ምርመራ
- ክትባቶች (መርፌዎች)
- የጥርስ ምርመራ
- የዓይን ምርመራ
- የመስማት ችሎታ ምርመራ
- የላብራቶሪ ምርመራ (የደም ውስጥ የሊድ መጠንን ጨምሮ)
- የባህሪ ጤና ምርመራ
- ሕክምና ወይም የአገልግሎት ሪፈራል
- የጤና ትምህርት

ለህክምና አስፈላጊ ከሆነ፡-

- አካላዊ፣ ኦኩፔሽናል፣ እና የንግግር ሕክምና(ቴራፒ)
- የዓይን እና የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች
- የባህሪ ጤና አገልግሎቶች
- መድሃኒቶች
- የሕክምና ቁሳቁሶች እና አቅርቦቶች

ከልጅዎ PCP ጋር መደበኛ ምርመራዎችን ማድረግ ለሚከተሉት ነገር ጠቃሚ ነው፦

- ልጅዎ ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ያግዛል
- የጤና ችግሮችን ቶሎ ለመለየት፣ እና
- በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የጤና ችግሮች እንዳይፈጠሩ ያደርጋል

ችግር እንዳለ ካሰቡ፣ ወዲያውኑ ለልጅዎ PCP ይደውሉ።

በነዚህ እድሜዎች ላይ ምርመራዎች እንዲደረጉ ይመከራል፥

| ጨቅላ ሕፃን | ድክ ድክ የሚል ህጻን ልጅ | ልጅ/ታዳጊ/ ወጣት አዋቂ |
|---|---|---|
| 1 ወር | 12 ወራት | በዓመት አንድ ጊዜ እድሚያቸው ከ 3 እስከ 20 ለሆኑ |
| 2 ወራት | 15 ወራት | |
| 4 ወራት | 18 ወራት | |
| 6 ወራት | 24 ወራት | |
| 9 ወራት | 30 ወራት | |

በተጨማሪ የHealthCheck (EPSDT) ወቅታዊ የጊዜ ሰሌዳ ቅጂ ለማግኘት፣ ሐኪምዎን መጠየቅ ይችላሉ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ፣ ወይም የእኛን ድረገጽ በ**wellpoint.com/dc/medicaid** መጎብኘት ይችላሉ። የጊዜ ሰሌዳው ልጅዎ ወደ ሐኪም መቼ መሄድ እንዳለበት ይነግርዎታል።

እንደ የHealthCheck/EPSDT አገልግሎቶች ጥቅማጥቅሞች አካል፣ ልጅዎ ከዚህ በታች ባለው "የተመዝጋቢ የጤና ጥቅማጥቅሞች" ክፍል ውስጥ የተገለጹትን ሌሎች የMedicaid ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት ይችላሉ።

**<u>የስደተኛ ቤተሰብ ልጆች ፕሮግራም</u>**

ልጅዎ በስደተኛ ቤተሰብ ልጆች ፕሮግራም ውስጥ ካለ/ች፣ ልጅዎ የደህና-ልጅ የእንክብካቤ አገልግሎቶችን ያገኛሉ። ይህ ፕሮግራም ልጅዎ 21 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ይቆያል።

ከደህና ልጅ እንክብካቤ በተጨማሪ፣ ልጅዎ ከታች ባለው "የተመዝጋቢ የጤና አገልግሎቶች" ክፍል ላይ የተገለጹትን ጥቅማጥቅሞች ያገኛሉ። ስደተኛ ልጆች የሕምና ኣገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ የሚሆኑት በWellpoint DC ተመዝግበው በሚቆዩበት ጊዜ ብቻ ነው።

**ለልጅዎ ለእነዚህ አገልግሎቶች ምንም መክፈል አይኖርብዎትም – ነጻ ናቸው። ማንኛውም ጥያቄዎች ካሎት ወይም ትራንስፖርት ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለማስያዝ እርዳታ ካስፈለጎት፣ እባክዎ የተመዘጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ833-359-1384 (TTY 711) ይደውሉ።**

**የልጅዎ የጥርስ ሕክምና**

ሁሉም የጥርስ ጤና ምርመራዎች እና ህክምናዎች ከ21 አመት በታች ለሆኑ Wellpoint DC ተመዝጋቢዎች ምንም ወጪ አይጠይቁም እና እያንዳንዱ ልጅ የመጀመሪያ ደረጃ የጥርስ ህክምና አቅራቢ ሊኖራቸው ይገባል።

የጥርስ ሐኪሞች የጥርስ መቦርቦርን ሊከላከሉ እና እርስዎ እና ልጅዎ ጥርሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባችሁ ሊያስተምሯችሁ ይችላሉ።

- ከልደት እስከ 3 ዓመት ድረስ፣ የልጅዎ PCP በመደበኛ የምርመራ ቀጠሮዎች ወቅት የአፍ ጤና ሕክምና ሊሰጡ ይችላሉ። PCP ልጁን ለጥርስ ሕክምና አገልግሎት ወደ ጥርስ ሀኪም መላክ አለበት።
- ከ 3 ዓመት ጀምሮ፣ ሁሉም ልጆች በየዓመቱ ለምርመራ በWellpoint መረብ ውስጥ ያለን የጥርስ ሐኪም ማየት አለባቸው። እባክዎ ለቀጠሮ የጥርስ ሐኪም ጋር ይደውሉ። የWellpoint DC አቅራቢ ማውጫ ውስጥ ወይም በመስመር ላይ በ **wellpoint.com/dc/medicaid** ላይ ይመልከቱ፣ በአቅራቢያዎ ያለ የጥርስ ሐኪም ለመምረጥ።

**<u>ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ያላቸው ህጻናት</u>**

ልጆች ቋሚ የሆኑ ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ የአካል፣ የእድገት፣ የባህርይ፣ ወይም የስሜት ሁኔታዎች ሲኖርባቸው፣ ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ልጆች ተጨማሪ የጤና ሕክምና እና ሌሎች አገልግሎቶች ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

Wellpoint DC ልጅዎ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸው መሆኑን ለማወቅ ሙሉ የጤና ምርመራ ለማድረግ እርስዎን ሊያገኙ ይችላሉ። Wellpoint DC እርስዎን ካላገኙ፣ እባክዎ የተመዘጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

ልጅዎ ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ካላቸው፥

- ልጅዎ ስፔሺያሊስት የሆነ PCP የማግኘት መብት አላቸው።
- የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለማገዝ ልጅዎ የጉዳይ አስተዳዳሪ ሊመደብላቸው ይችላል።
- የልጅዎ የጉዳይ አስተዳዳሪ የሕክምና እቅድ ለማዘጋጀት ከእርስዎ እና ከልጅዎ ሐኪም ጋር ይሰራሉ።

እርስዎ እና የልጅዎ ሐኪም የልጅዎን የሕክምና እቅድ መፈረማችሁን ያረጋግጡ። እርስዎ የሕክምና እቅድ ከሌሎት፣ ለልጅዎ የሕክምና እቅድ ለመጠየቅ ወደ Wellpoint የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ይደውሉ።

**የIDEA ፕሮግራም**

IDEA የፌደራል ህግ ነው። IDEA ማለት የአካል ጉድለት ያለባቸው ሰዎች የትምህርት ህግ ማለት ነው። የIDEA ፕሮግራም የእድገት መዘግየት፣ የአካል ጉድለት፣ ወይም ልዩ ፍላጎቶች ላለው ልጅዎ ልዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። እድሜያቸው እስከ 3 የሆናቸው ልጆች ከWellpoint DC የቀደመ የጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ያገኛሉ። እድሜያቸው 4 እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ልጆች ከዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት እና የህዝብ ቻርተር የትምህርት ቤቶች ስርዓት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ያገኛሉ።

በDC የእድገት ቻርት (የተያያዘውን ይመልከቱ) ልጅዎ የእድገት መዘግየት ያለባቸው መሆን አለመሆኑን ለመለየት ይረዳዎታል።

## የእድገት ሰንጠረዥ (ቻርት)

የአካል ጉድለት ላለባቸው ግለሰቦች የትህምርት ህግ (IDEA) ፕሮግራም የእድገት መዘግየት፣ የአካል ጉድለት፣ ወይም ልዩ ፍላጎቶች ላለው ልጅዎ ልዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። እድሜያቸው እስከ 3 የሆናቸው ልጆች ከWellpoint DC የቀደመ የጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ያገኛሉ። እድሜያቸው 4 እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ልጆች ከዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት እና የህዝብ ቻርተር የትምህርት ቤቶች ስርዓት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ያገኛሉ።

የእድገት ሰንጠረዡ(ቻርቱ) ልጅዎ የእድገት መዘግየት ያለባቸው መሆን አለመሆኑን ለመለየት ይረዳዎታል። እንደ መመሪያ ይጠቀሙበት። ልጅዎ እነዚህን የእድገት ደረጃዎች ላይ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ላይ ካሉ ልጆች ትንሽ ቀደም ወይም ዘግየት ብሎ ሊደርስ ይችላል። ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካዎት፣ የልጅዎን ሐኪም ያነጋግሩ።

የጉዳይ አስተዳዳሪዎቻችን ስለ IDEA እና ልጅዎ ማግኘት ስለሚችሉት ሌሎች አገልግሎቶች የበለጠ ሊነግርዎ ይችላሉ።

የሚከተሉት ልጅዎ በሚያድግበት ጊዜ ሊያስተውሏቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ናቸው።

| | |
|---|---|
| **በ 7 ወራት መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• ስማቸው ሲጠራ ጭንቅላታቸውን ማዞር<br>• ለሌላ ሰው ፈገግ ማለት<br>• ለድምጾች በድምጽ ምላሽ መስጠት<br>• እንደ peek-a-boo(ፒከኤቡ) ባሉ ማህበራዊ ጨዋታዎች መደሰት | **በ 2 ዓመት (24 ወራት) መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• ከ 2-4-ቃላት ያላቸውን ሀረጎችን መጠቀም<br>• ቀላል መመሪያዎችን መከተል<br>• በሌሎች ልጆች የበለጠ ፍላጎት ማሳየት<br>• አንድ እቃ ወይም ስእል ሲጠራ ማመልከት |
| **በ 1 ዓመት (12 ወራት) መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• ቀላል የእጅ ምልክቶችን መጠቀም (በማውለብለብ "ቻው-ቻው" ማለት)<br>• እንደ “ማ” እና “ዳ” ያሉ ድምጾችን ማውጣት<br>• በጨዋታቸው ውስጥ የሌሎችን ድርጊቶች ማስመሰል (ሲያጨበጭቡ ማጨብጨብ)<br>• “አይሆንም” ሲባሉ ምላሽ መስጠት | **በ 3 ዓመት (36 ወራት) መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• አብረዋቸው ለሚጫወቱ ሰዎች ፍቅር ማሳየት<br>• ከ 4-5-ቃላት ያላቸውን አረፍተነገሮችን መጠቀም<br>• አዋቂዎችን እና ጓደኞችን ማስመሰል (ሌሎች ልጆች ሲሮጡ መሮጥ)<br>• በአሻንጉሊት፣ እንስሳት እና ሰዎች እቃ እቃ መጫወት (ቴዲ ቢርን “መመገብ”) |
| **በ 1 ½ ዓመት (18 ወራት) መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• ቀላል የማስመሰል ጨዋታ መጫወት (በአሻንጉሊት ስልክ ላይ “ማውራት”)<br>• ትኩረት ወደሚስቡ ነገሮች ማመልከት<br>• አንድ እቃ ላይ ሲጠቁሙ ወይም እንዲመለከቱ ሲነግሯቸው መመልከት<br>• ያለምንም ግፊት ብዙ ነጠላ ቃላትን መጠቀም | **በ 4 ዓመት (48 ወራት) መጨረሻ ላይ፣ አብዛኛው ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**<br>• ከ 4-6-ቃላት ያላቸውን አረፍተነገሮችን መጠቀም<br>• ባለ 3-ደረጃ ትእዛዞችን መተግበር (“ልበስ/ሺ፣ ጸጉር አበጥር/ሪ፣ እና ፊትህ/ሽን ታጠብ/ቢ”)<br>• ከሌሎች ልጆች ጋር መተባበር |

ልጅዎ ማደግ ባለባቸው ሁኔታ እያደጉ ካልሆነ፣ ልጅዎ እንዲመረመር ያድርጉ (“IDEA ግምገማ”)። የ IDEA ግምገማ ለማግኘት፣ የርስዎ PCP ጋር ይደውሉ። ልጅዎ የIDEA አገልግሎቶች የሚያስፈልጓቸው ከሆነ፣ የእርስዎ PCP ልጅዎን ወደ ዲሲ ስትሮንግ ስታርት (DC Strong Start) የቀደመ የጣልቃገብነት ፕሮግራም ይልኳቸዋል።

Wellpoint DC ስለ IDEA እና ልጅዎ ማግኘት ስለሚችሉት ሌሎች አገልግሎቶች የበለጠ ሊነግርዎ የሚችሉ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች አሉት።

Wellpoint DC ልጅዎ ለቀደመ የጣልቃገብነት አገልግሎቶች ብቁ ከሆነ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ አገልግሎቶች ሽፋን ይሰጣል፦

- እድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ልጆች፣ አገልግሎቱ በልጅዎ የሕክምና እቅድ (ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP) ውስጥ የተካተተ ቢሆንም እንኳን Wellpoint DC የልጅዎን ሁሉንም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ይሸፍናል።
- እድሜያቸው 3 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልጆች፣ Wellpoint DC፦
    - ልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ በማይሆንበት ጊዜ ለሚያስፈልገው ሁሉም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እና በልጅዎ የሕክምና እቅድ ውስጥ ላሉ አገልግሎቶች ይከፍላል—በምሽት፣ በሳምንቱ የእረፍት ቀናት፣ እና የበዓላት ቀናትን ጨምሮ።
    - በትምህርት ቤቱ የሕክምና እቅድ አማካኝነት የማይሰጡ አገልግሎቶችን ያስተባብራል።

ልጅዎ በIDEA ፕሮግራም አማካኝነት ሊያገኙት ስለሚችሉ አገልግሎቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶችን **833-359-1384 (TTY 711)** ወይም የልጅዎን ትምህርት ቤት ያግኙ።

**ክትባቶች (መርፌዎች) ለልጆች እና ወጣቶች**

ልጅዎን ጤናማ አድርጎ ለማቆየት ክትባቶች (መርፌዎች) ጠቃሚ ናቸው። ልጅዎ በጣም ህጻን በሆነበት ጊዜ፣ ልጅዎ ክትባቶቹን በየጥቂት ወራት ያስፈልጋቸዋል። ክትባቶቹ የሚጀምሩት ሲወለዱ ነው። እነዚህ ክትባቶች ከበሽታ ይጠብቋቸዋል።

የእርስዎ PCP እና Wellpoint DC ለልጅዎ ክትባቶች ቀጠሮ ያስይዙላቸዋል።
የክፍለጊዜ ቻርት (የገባውን ይመልከቱ) የልጅዎን ክትባቶች በሚመለከት የጊዜ ሰሌዳ።

## የሚመከር የልጆች የክትባት (መርፌ) መርሃ ግብር

ልጅዎ በወቅቱ ክትባቱን እንዲያገኝ አስፈላጊ ነው። እነዚህን እርምጃዎች ይከተሉ፦

1. የእሱ ወይም የእሷ PCP ልጅዎ መርፌ(ሾት) እንደሚያስፈልጋቸው ሲናገሩ ወደ ሐሚም መውሰድ።
2. ልጅዎ የሚያስፈልጋቸውን ክትባቶች(ሾት) ለመከታተል እንዲረዳዎ የሚከተለውን ሰንጠረዥ(ቻርት) እንደ መመሪያ ይጠቀሙ።

እንዲሁም ለማንበብ ቀላል የሆኑ ለሁሉም የእድሜ ክልሎች የሚሆኑ የክትባት ሰንጠረዦችን የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ማዕከላት(CDC) ድረገጽ በ cdc.gov/vaccines/schedules ላይ ማግኘት ይችላሉ።

| **ከልደት እስከ 3 ዓመት** | |
|---|---|
| **ዕድሜ** | **ክትባት** |
| መወለድ | HepB #1 |
| 2 ወራት | HepB#2, DTaP#1, RV#1,<br>Hib#1, PCV#1, IPV#1 |
| 4 ወራት | DTaP#2, RV#2, Hib#2,<br>PCV#2, IPV#2 |
| 6 ወራት | HepB#3, Hib#3, DTaP#3,<br>RV#3, PCV#3, IPV#3 |
| 12 ወራት | HiB#4, MMR#1, Varicella #1,<br>PCV#4<br>HepA#1 |
| 15 ወራት | ቫሪሴላ #2 ወይም 2ኛ ዶዝ (መጠን) 4 ዓመታቸው ሊሰጥ ይችላል |
| 18 ወራት | Hep A#2 |
| **ዕድሜ 4-12** | |
| ዕድሜ 4-6 | DTaP፣ MMR፣ IPV |
| ዕድሜ 11-12 | HPV፣ MCV4 |
| ዕድሜ 13 ወይም ከዚያ በላይ | Varicella |
| **ዕድሜ 13-18** | |
| ዕድሜ 13-18 | Tdap፣ HPV |
| ዕድሜ 18 ወይም ከዚያ በታች | MCV4 |
| **ከ6 ወር ጀምሮ** | |
| በየዓመቱ | ወቅታዊ የኢንፍሉዌንዛ ("ፍሉ") ክትባቶች በየዓመቱ በሚሰጠው ምክረሀሳብ መሰረት |

## የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች

### ሽፋን የሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች በWellpoint DC

ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር ለሁሉም የWellpoint DC ተመዝጋቢዎች የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶችን እና ጥቅሞችን ያሳያል። ለአንዳንድ ጥቅማጥቅሞች፣ የተወሰነ የእድሜ ገደብ ላይ መሆን ወይም ለአገልግሎቱ የተወሰነ ፍላጎት ሊኖርዎት ይገባል። Wellpoint DC በመረብ ውስጥ ወዳለ አቅራቢ ወይም ሆስፒታል ከሄዱ፣ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ማንኛውም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ አያስከፍልዎትም።

እርስዎ Wellpoint DC የተወሰኑ የጤና እንክብካቤን የሚሸፍን መሆኑን ወይም እነዚህን አገልግሎቶች እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ጥያቄ ካሎት፣ ወደ Wellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት | ይህን ጥቅማጥቅም ማን ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| **የአዋቂ የጤንነት ምርመራ አገልግሎቶች** | • ክትባቶች<br>• በግብረስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች መደበኛ የማጣሪያ ምርመራ<br>• HIV/AIDS ማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ምክር<br>• የጡት ካንሰር ምርመራ<br>• የማህጸን ካንሰር ምርመራ (ለሴቶች ብቻ)<br>• የኦስቲዮፖሮሲስ (አጥንት መሳሳት) ምርመራ (ለድህረ ማረጥ ለሴቶች)<br>• የ HPV ምርመራ<br>• የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ (ለወንዶች ብቻ)<br>• የአብዶሚናል አኦርቲክ አኑሪዝም ምርመራ<br>• ከመጠን ያለፈ ውፍረት ምርመራ<br>• የስኳር በሽታ ምርመራ<br>• የከፍተኛ የደም ግፊት እና ኮሌስትሮል (የሊፒድ በሽታ) ምርመራ<br>• የድብርት ምርመራ<br>• የኮሎሬክታል ካንሰር ምርመራ (እድሜያቸው 50 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች)<br>• ሲጋራ የማጨስ የምክር አገልግሎት<br>• የምግብ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የምክር አገልግሎት<br>• የባህሪ ጤና የምክር አገልግሎት<br>• የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ ምርመራ | እንደ አግባብነቱ እድሜያቸው ከ 21 በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች |
| **የባህሪ ጤና አገልግሎቶች** | • የምርመራ ግምገማ<br>• የሐኪም ጉብኝቶች<br>• የግል የምክር አገልግሎት<br>• የቡድን የምክር አገልግሎት<br>• የቤተሰብ የምክር አገልግሎት<br>• በፌዴራል ደረጃ ብቁ የሆነ የጤና ማእከል (FQHC) አገልግሎቶች<br>• የመድሃኒት ቀውስ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |

| | | |
|---|---|---|
| • **የአእምሮ ጤና** | • ሆስፒታል ውስጥ የተኙቶ ታካሚ እና የድንገተኛ ዲፖርትመንት አገልግሎቶች<br>• የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎቶች<br>• እርግዝናን ሊያወሳስብ የሚችል ማንኛውም የአእምሮ ሁኔታ ሕክምና<br>• የታካሚ ሳይኪያትሪክ ሬዚዴንሺያል ሕክምና የተቋም አገልግሎቶች (PTRF) እድሜያቸው ከ 22 በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች ለተከታታይ ሰላሳ (30) ቀናት<br>• በ ግለሰባዊ ትምህርት እቅድ (IEP) ወይም ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) ውስጥ ለተካተቱ ህጻናት ትምህርት ቤት መሰረት ያደረጉ የባህሪይ ጤና አገልግሎቶች፣ በበዓል ቀናት፣ በትምህርት እረፍት ቀናት፣ ወይም ልጁ በህመም ምክንያት ትምህርት ቤት በማይኖርበት ቀናት<br>• የባህሪ ጤና እና የአደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀም አገልግሎቶች በማንኛውም የቀን መቁጠሪያ ወር ውስጥ እስከ 15 ቀናት ድረስ በአእምሮ ህመም ተቋም ውስጥ | |
| • **የሱስ አጠቃቀም በሽታ (SUD)** | • የምርመራ ግምገማ<br>• የቀውስ አገልግሎቶች<br>• የምክር አገልግሎት<br>• ሳይኮቴራፒ<br>• የቴራፒ ቡድኖች<br>• በመድሃኒት የታገዘ ህክምና<br>• የውስጥ-ታካሚ መውጣት ቁጥጥር/ መርዝ ከሰውነት ማውጣት<br>• የመኖሪያ ቤት ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች፣ እንደ አግባብነቱ |
| **የልጅ የደህንነት ምርመራ አገልግሎቶች** | የታመሙ ልጆችን ለመንከባከብ እና የጤናማ ልጆች ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ማንኛውም ነገሮች፣ የሚከተሉትን የማጣሪያ ምርመራ እና ግምገማዎችን ጨምሮ፥<br>• የጤና እና የእድገት ታሪክ እና የማጣሪያ ምርመራዎች<br>• የአካላዊ እና የባህርይ ጤና እድገት እና ምርመራዎች<br>• አጠቃላይ የጤና ምርመራ<br>• ክትባቶች<br>• የላብራቶሪ ምርመራዎች፣ የደም ውስጥ የሊድ መጠንን ጨምሮ<br>• የጤና ትምህርት/የመጠባበቅ መመሪያ<br>• የጥርስ ምርመራ አገልግሎቶች<br>• የዓይን ምርመራ አገልግሎቶች<br>• የመስማት የምርመራ አገልግሎቶች | ተመዝጋቢዎች እድሜያቸው ከ 21 በታች የሆኑ |

| | | |
|---|---|---|
| | • የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት<br>• የባህሪ ጤና አገልግሎቶች<br><br>*በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጅ የሚሰጡ ማንኛውም የጤና አገልግሎቶችን አያካትትም | |
| **የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች** | • አጠቃላይ የጥርስ ሕክምና (መደበኛ እና ድንገተኛ ሕክምናን ጨምሮ) እና ለልዩ ችግሮች የኦርቶዶንቲክ ሕክምና<br>• እድሜያቸው ከ 3 እስከ 20 ለሆኑ ልጆች የጥርስ ሐኪም ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረጉ ጉብኝቶች ሽፋን አላቸው<br>• የልጅ PCP እድሜያቸው እስከ 3 የሆኑ ልጆችን የጥርስ ምርመራ ሊያከናውን ይችላል።<br>• መደበኛ የኦርቶዶንቲክ ሕክምናን አያካትትም<br>• በዓመት እስከ አራት (4) ጊዜ ያክል የፍሎራይድ ቫርኒሽ ሕክምና<br>• መሸፈኛ ማድረግ | እድሜያቸው ከ 21 በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች<br><br>እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች ከ Medicaid የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። ለMCP የጥርስ ህክምና መስመር ይደውሉ በ866-758-6807 |
| | • አጠቃላይ የጥርስ ምርመራዎች እና መደበኛ የጥርስ ማጽዳት በየስድስት (6) ወራት<br>• የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና ጥርስ ማውለቅ<br>• ድንገተኛ የጥርስ ሕክምና<br>• መሞላት<br>• ኤክስሬይ (በየሶስት (3) ዓመቱ አንድ (1) ጊዜ ብቻ የተሟላ ተርታ)<br>• በመላ አፍ ውስጥ ያሉ የበሰበሱ ነገሮችን ማስወገድ<br>• የአፍ ፕሮፊላክሲስ በዓመት እስከ ሁለት (2) ጊዜ ብቻ የተገደበ<br>• ተከታታይ የጥርስ መንከስ<br>• የማስታገሻ ሕክምና<br>• የስር ቦይ ሕክምና<br>• የጥርስ ክራውን<br>• የተጎዱ ጥርሶችን መንቀል<br>• ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወልቅ ፕሮስቴሲስ (አንድ ወይም ከዚያ በላይ የወለቁ ጥርሶችን የሚተካ ማንኛውም የጥርስ መሳሪያ ወይም እቃ፣ አስፈላጊ ከሆነ የሚወልቅ እና መልሶ የሚተከል ተያያዥ ቅርጾችን ጨምሮ) ማድረግ በየአምስት (5) ዓመታት አንድ ጊዜ። የተወሰኑ ገደቦች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ።<br>• ሆስፒታል ተኝቶ የሚደረግ ማንኛውም የጥርስ ሕክምና አገልግሎት የቀደመ ፈቃድ (ቅድመ ፈቃድ) ሊኖረው ይገባል<br>• በምርጫ የሚደረግ የቀዶ ጥገና ሕክምና አጠቃላይ ማደንዛዥን የሚጠይቅ | እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

| | | |
|---|---|---|
| **የዳይሊሲስ (የኩላሊት እጥበት) አገልግሎቶች** | • በሳምንት እስከ 3 ጊዜያት ሕክምና (በቀን ለአንድ ጊዜ የተገደበ) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ_(DME) እና አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS)** | • ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)<br>• አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች** | • የጤና ሁኔታዎ የማጣሪያ ምርመራ፣ የድህረ ማገገም አገልግሎቶች፣ እና ድንገተኛ የሕክምና ሁኔታ ካለብዎ የማረጋጋት አገልግሎቶች፣ አቅራቢው በWellpoint DC መረብ ውስጥም ሆነ ውጪ ቢሆንም እንኳን<br>• የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | • የእርግዝና ምርመራ፤ ለሴቷ የምክር አገልግሎት<br>• መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ<br>• እድሜያቸው ከ 21 በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ማምከን (ከቀዶ ጥገናው 30 ቀናት በፊት የተመዝጋቢው ፊርማ ያለው የጸደቀ የማምከን ቅጽ ያስፈልጋል)<br>• የማጣሪያ ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት፣ እና ክትባቶች (ለ Human Papilloma Virus- HPV ጨምሮ)<br>• በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ እና የመከላከል ሕክምና<br>• ነርስ አዋላጅ ሐኪም እና የዳውላ አገልግሎቶች<br><br>*እድሜያቸው ከ 21 በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎችን የማምከን የቀዶ ጥገናን አያካትትም | ሁሉም ተመዝጋቢዎች፣ እንደ አግባብነቱ |
| **የመስማት ጥቅማጥቅሞች** | • ከመስማት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ የመስሚያ መሳሪያዎች እና የመስሚያ መሳሪያ ባትሪዎች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች** | በቤት ውስጥ የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦<br>• የነርሲንግ እና የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ እንክብካቤ<br>• በቤት ጤና ኤጀንሲ የሚሰጥ የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ አገልግሎቶች<br>• የአካል ህክምና፣ አኩፔሽናል ቴራፒ፣ የንግግር ፓቶሎጂ እና የኦዲዮሎጂ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የሆስፒስ እንክብካቤ** | • ወደ ሕይወት መጨረሻ የተቃረቡ ሰዎች የድጋፍ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የሆስፒታል አገልግሎቶች** | • የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች (የመከላከል፣ የመመርመሪያ፣የሕክምና፣የማገገሚያ ወይም የማስታገሻ አገልግሎቶች) | ከራሳቸው PCP ሪፈራል ያላቸው ወይም ድንገተኛ ሁኔታ ላለባቸው ማንኛውም ተመዝጋቢዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | • የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች (የሆስፒታል ቆይታ) | |
| **የላብራቶሪ እና የኤክስሬይ አገልግሎቶች** | • የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ኤክስሬዮች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የነርሲንግ ሆም እንክብካቤ** | • በነርሲንግ ሆም ውስጥ በሰለጠኑ ነርስ የሙሉ ጊዜ እንክብካቤ ለተከታታይ 90 ቀናት ድረስ ያክል | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የግል እንክብካቤ አገልግሎቶች** | • ለተመዝጋቢው የተመዝጋቢው ቤተሰብ አባል ባልሆነ ብቁ ሰው የሚሰጡ እንዲህ ያሉ አገልግሎቶች፣ አብዛኛውን ጊዜ ቤት ውስጥ እና የተመዝጋቢው የሕክምና እቅድ አካል የሆነ በሐኪም የተፈቀደ።<br>• ለዚህ አገልግሎት ቅድመ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልግዎታል | ሁሉም ተመዝጋቢዎች ሆስፒታል ወይም ነርሲንግ ሆም ላሉ ተመዝጋቢዎች አይኖርም። |
| **የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች (የሃኪም ማዘዣ ያላቸው መድሃኒቶች)** | • በWellpoint DC የመድሃኒት ቅጽ ላይ ያሉ በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች። የመድሃኒት ቅጹን በ **wellpoint.com/dc/medicaid** ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በመደወል ማግኘት ይችላሉ።<br>• በመረብ ውስጥ ያሉ መድሃኒት ቤቶች ውስጥ ያሉ መድሃኒቶችን ብቻ ያካትታል።<br>• የሃኪም ማዘዣ የማያስፈልጋቸው (መደብር ውስጥ የሚሸጡ) መድሃኒቶችን ያካትታል ። በመረብ ውስጥ ያሉ መድሃኒት ቤቶች ውስጥ ያሉ መድሃኒቶችን ብቻ ያካትታል። የሚከተሉትን ያካትታል<br>የሐኪም ማዘዣ የማያስፈልጋቸው (መደብር ውስጥ የሚሸጡ) መድኃኒቶች፣ የሚከተሉትን የሚያካትት ነገር ግን በነዚህ ብቻ ያልተገደበ፥ የሚዋጥ የሕመም ማስታገሻ መድኃኒቶች አንድ ገቢር ንጥረ ነገር ያለው (እንደ አስፕሪን ፣ አሲታሚኖፊን እና አይብሮፊን)፣ ፊሮስ ሶልት፤ እስከ ሶስት የሚደርሱ ንጥረነገሮች ያላቸው አንቲአሲዶች (እንደ አሉሚኒየም፣ ማግኒዚየም፣ እና ቢስመት)፤ የስኳር በሽታ ጋር የተያያዙ ነገሮች(እንደ ኢንሱሊን እና ሲሪንጅ)፤ የህጻናት፣ የቅድመ ወሊድ፣ እና የአረጋዊያን ቫይታሚኖች፤ የቤተሰብ ምጣኔ መድሃኒቶች እና አቅርቦቶች (ድንገተኛ የወሊድ መከላከያዎች፣ ኮንዶሞች/ዳያፍራሞች)፤ እና Senna extract (የሴና ኤክስትራክት)። ሙሉ ዝርዝር በድረገጹ ላይ ይኖራል ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በመደወል ይገኛል። በመደብር ውስጥ የሚሸጡ | ለሁለቱም ብቁ ከሆኑት ውጪ ያሉ ሁሉም ተመዝጋቢዎች (Medicaid/Medicare)<br><br>የሃኪም ማዘዣቸው በ Medicare ክፍል D የሚሸፈን ተመዝጋቢዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | መድሃኒቶችን ለማግኘት ከሐኪምዎ የሃኪም ማዘዣ ማግኘት አለብዎ። | |
| **የእግር በሽታ ሐኪም** | • ለእግር ችግሮች ልዩ ሕክምና<br>• በሕክምና አስፈላጊ ሲሆን መደበኛ የእግር ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ዋና የእንክብካቤ አገልግሎቶች** | የመከላከል፣ ቀላል፣ እና ከባድ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በአጠቃላይ በእርስዎ PCP የሚሰጥ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የፕሮስቴቲክ መሳሪያዎች** | • ፈቃድ ባለው አቅራቢ የታዘዙ የምትክ፣ የማስተካከያ፣ ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የማገገሚያ አገልግሎቶች** | የአካል፣ የንግግር፣ እና ኦኩፔሽናል ቴራፒን ጨምሮ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የስፔሺያሊስት አገልግሎቶች** | • ልዩ ስልጠና በወሰዱ ሐኪሞች ወይም የላቀ ልምድ ባላቸው ነርሶች የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>• ሪፈራል አብዛኛውን ጊዜ ያስፈልጋል<br>• በቀዶ ጥገና ወይም በበሽታ ምክንያት የተፈጠረ፣ በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ወይም የተፈጥሮ አካል ጉድለትን፣ ወይም መደበኛ የሰውነት አሰራርን የሚያጎድል ሁኔታን ለማስተካከል ካልሆነ በስተቀር የኮስሜቲክ አገልግሎቶችን እና ቀዶ ጥገናዎችን አያካትትም | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ ከህክምና ቀጠሮዎች እና ከዚያ መልስ መጓጓዣ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የዓይን ሕክምና** | • የዓይን ምርመራዎች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እና እንደ አስፈላጊነቱ፤ እና የዓይን መነጽሮች (የማስተካከያ ሌንሶች) እንደ አስፈላጊነቱ | ተመዝጋቢዎች እድሜያቸው ከ 21 በታች የሆኑ |
| **የዓይን ሕክምና** | • በየሁለት (2) ዓመቱ አንድ (1) ጥንድ መነጽሮች ተመዝጋቢው የአይን መነጽራቸው ካልጠፋባቸው ወይም ማዘዣው ከ 0.5 ዳዮፕትር በላይ ካልተቀየረ በስተቀር | እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

**ከፍያቸውን የማንሸፍነው አገልግሎቶች**

- ኮስሜቲክ የቀዶ ጥገና
- የሙከራ ወይም የምርመራ አገልግሎቶች፣ የቀዶ ጥገናዎች፣ ሕክምናዎች፣ እና መድሃኒቶች
- የክሊኒካል ሙከራ ፕሮቶኮል አካል የሆኑ አገልግሎቶች
- ጽንስ ማስወረድ፣ ወይም በፈቃደኝነት ጽንስን ማቋረጥ፣ በፌደራል ህጉ መሰረት የሚቻል አይደለም
- እድሜያቸው ከ 21 በታች ለሆኑ ሰዎች የማምከን አገልግሎቶች
- በሕክምና አስፈላጊ ያልሆኑ አገልግሎቶች
- የተወሰኑ የምክር ወይም የሪፈራል አገልግሎቶች በሃይማኖታዊ ወይም የሞራል እምነቶች ምክንያት በWellpoint DC ሽፋን ላይሰጣቸው ይችላል። ለበለጠ መረጃ DHCFን በ 202-442-5988 ያግኙ።

**የህክምና ሽግግር**

Wellpoint DC ለእርስዎ አዲስ ከሆነ፣ ለመጀመሪያ 90 ቀናት የተያዙትን የሐኪም ቀጠሮዎች እና የመድሃኒት ማዘዣዎችን እንዳሉ መቆየት ይችላሉ። አቅራቢዎ በአሁን ወቅት በWellpoint DC መረብ ውስጥ ካልሆኑ፣ በWellpoint DC የአቅራቢ መረብ ውስጥ ያለ አዲስ አቅራቢ እንዲመርጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

ሐኪምዎ የWellpoint DC መረብን ከለቀቁ፣ ሌላ አቅራቢ ለመምረጥ ጊዜ እንዲኖርዎ በ 15 የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። Wellpoint DC አቅራቢዎን ካቋረጠ፣ የሚያበቃበት ጊዜ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት በ 30 የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን።

## ማወቅ ያለብዎ ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች

**ቦታ ከቀየርኩ ምን ማድረግ ይኖርብኛል**

- የመገኛ መረጃዎን በመስመር ላይ በ districtdirect.dc.gov ወቅታዊ ያድርጉ።
- እባክዎ የተመዘገቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በWellpoint DC 833-359-1384 (TTY 711)።

**ህጻን ልጅ ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።
- እባክዎ የተመዘገቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በWellpoint DC 833-359-1384 (TTY 711)።

**ህጻን ልጅ በማደጎ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።

**ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።
- እባክዎ የተመዘገቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በWellpoint DC 833-359-1384 (TTY 711)።

**የእኔን MCP እንዴት መቀየር እንደምችል**

- የእርስዎን MCP በሚከተለው ሁኔታ መቀየር ይችላሉ፥
  - የመጀመሪያው የምዝገባ ቀንዎን ተከትሎ ባሉት 90 የካላንደር ቀናት ወይም ከዲስትሪክቱ የምዝገባ ማስታወቂያዎ ከደረሶት ከ 90 የካላንደር ቀናት በኋላ፣ ኋለኛው የሆነው የትኛውም።
  - በክፍት የምዝገባ ወቅት በዓመት አንድ ጊዜ።
  - ጊዜያዊ የብቃት ማጣት ክፍት የምዝገባ ወቅቱ እንዲያመልጥዎ ካደረገ።
  - ዲስትሪክቱ MCP ላይ ቅጣት ከጣለ ወይም ምዝገባውን ካገደ።
  - ጥሩ ምክንያት/ሰበብ ካሎት በማንኛውም ጊዜ፣ ለምሳሌ፥
    - ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ ከሆኑ፤
    - Wellpoint DC በሞራል ወይም ሐይማኖታዊ ተቃውሞዎች ምክንያት፣ የሚያስፈልግዎትን አገልግሎት(ቶች) ካልሸፈነ፤
    - እርስዎ ተያያዥ አገልግሎቶችን በተመሳሳይ ጊዜ እንዲከናወን ከፈለጉ፣ እና ሁሉም ተያያዥ አገልግሎቶች ካልተገኙ፣ እና አቅራቢዎ አገልግሎቶቹን ለየብቻ ማግኘት አስጊ ነው ብለው ከወሰኑ።
    - MCP የእርስዎን ዘር፣ ጾታ፣ ብሄር፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ሐይማኖት፣ የአካል ጉድለት፣ እርግዝና፣ እድሜ፣ የጄኔቲክ መረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታዊ መለያ፣ የግል አቀራረብ፣ የቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ የፖለቲካ ዝንባሌ፣ እና የገቢ ምንጭ ወይም የመኖሪያ አድራሻን መሠረት በማድረግ አድልዎ እንደፈጸሙብዎ ካመኑ፤ ወይም
    - ደካማ ጥራት ያለው ሕክምና ያገኙ ሆኖ ከተሰማዎት፣ ሽፋን ላላቸው አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፣ ወይም የእርስዎ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ላይ ልምድ ያላቸው አቅራቢዎች ተደራሽ እንዳልሆኑ ከተሰማዎት።
- የD.C. ጤናማ ቤተሰቦች (D.C. Healthy Families) ከክፍት የምዝገባ ወቅት ሁለት ወራት በፊት ደብዳቤ ይልክልዎታል። ደብዳቤው MCPዎችን እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ይነግርዎታል።
- የእርስዎን MCP ሲቀይሩ፣ የሚያስፈልግዎን እንክብካቤ ማግኘት እንዲቀጥሉ የእርስዎ የጤና እንክብካቤ መረጃዎ ወደ መረጡት አዲስ MCP ይሸጋገራል።

**ከዚህ በኋላ የሚከተሉትን ካደረጉ ከWellpoint DC የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ አይፈቀድልዎትም፥**

- የ Medicaid ብቃትዎን ካጡ
- የማህበራዊ ዋስትና ገቢ (SSI) ብቃትዎን ካረጋገጡ

**ልጁ/ጅቷ ከWellpoint DC በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሰረዛሉ፥**

- በዲስትሪክቱ ጥበቃ ሥር ከሆነ

**የD.C. መንግስት በሚከተሉት ምክንያቶች እርስዎን ከWellpoint DC ሊያስወጣዎት ይችላል፥**

- የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ካደረጉ፤
- የሜዲኬይድ የማጭበርበር ወንጀልን ከፈጸሙ፤ ወይም
- የተመዝጋቢ ግዴታዎችዎን ካላከበሩ።

### ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ሲደርሰኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ለሆነ ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ከደረሰዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**።

### ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች መክፈል

- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ማግኘት እንዳለብዎ ከወሰኑ እና ከWellpoint DC የጽሁፍ ፈቃድ ከሌሎት፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ መክፈል ይኖርብዎታል።
- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ለማግኘት ከወሰኑ፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ እንደሚከፍሉ መስማማትዎን የሚገልጽ መግለጫ መፈረም አለብዎ።
- አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ ***በፊት*** የተመዝጋቢ ID ካርድዎን ማሳየት ያስታውሱ እና ለሐኪሞችዎ የWellpoint DC ተመዝጋቢ መሆንዎን መንገር ሁሉጊዜ ያስታውሱ።

### የቀደመ መመሪያ

የቀደመ መመሪያ ማለት የጤና እንክብካቤ ምርጫዎችዎን ሌሎች እንዲያውቁት ለማድረግ የሚያስችል እርስዎ የሚፈርሙት ሕጋዊ ሰነድ ነው። እርስዎ ስለራስዎ መናገር በማይችሉበት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህ "ቋሚ ኑዛዜ" ወይም "ዘላቂ የውክልና ሥልጣን" ተብሎ ይጠራል።

የቀደመ መመሪያ የሕክምና እንክብካቤዎን አስመልክቶ ምርጫዎችን የሚያደርግ ሰው እንዲመርጡ ያስችልዎታል። በተጨማሪ የቀደመ መመሪያ ፍላጎቶችዎን ለሌሎች ለመንገር በማያስችል ሁኔታ በጣም ቢታመሙ ምን ዓይነት የሜዲካል ሕክምና ማግኘት እንደሚፈልጉ ለመናገር ያስችልዎታል።

ስለ ቀደመ መመሪያዎ ከቤተሰብዎ፣ ከእርስዎ PCP፣ ወይም እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ እርስዎን ከሚያግዙ ሌሎች ሰዎች ጋር ማውራት ጠቃሚ ነው።

የቀደመ መመሪያ መሙላት እና መፈረም ከፈለጉ፣ ቀጣይ ቀጠሮዎ ላይ የእርስዎ PCP እንዲያግዝዎ ይጠይቋቸው፣ ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**፣ እና እነሱ እርስዎን ያግዛሉ።

### ሌላ መድን ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ

እርስዎ የWellpoint DC ተመዝጋቢ ከሆኑ፣ ማንኛውም ሌላ የጤና መድን ካለዎት ወዲያውኑ ሊነግሩን ይገባል። እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**።

**ማጭበርበር ምንድን ነው?**

ማጭበርበር ከባድ ጉዳይ ነው። ማጭበርበር ማለት የማይገባዎትን የተወሰነ ጥቅማጥቅምን ወይም ክፍያን ለማግኘት ሀሰተኛ መግለጫዎችን ወይም ፍሬ ነገሮችን መግለጽ ማለት ነው። የአቅራቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ፥ ላልተሰጡ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ። የተመዝጋቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ ማለት የColumbia ዲስትሪክት ዙሪያ ውጪ እየኖሩ Columbia ውስጥ እንደሚኖሩ በሐሰት መግለጽ።

የማጭበርበር ድርጊትን ከጠረጠሩ፣ እባክዎ ለኛ ያሳውቁን። እራስዎን መግለጽ ወይም ስምዎን መስጠት አያስፈልግዎትም። ማጭበርበርን ሪፖርት ለማድረግ፣ ይደውሉ ወደ Wellpoint DC የትግበራ የስልክ መስመር ጋር፣ 866-847-8247 ወይም የDC የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ ማጭበርበር ዲፖርትመንት የስልክ መስመር ጋር በ877-632-2873 ይደውሉ። ስለ ማጭበርበር የበለጠ መረጃ ከፍለጉ፣ የWellpoint DC ድረገጽን በ **wellpoint.com/dc/medicaid** ይጎብኙ።

**የሐኪም (ዶክተር) የጥቅማጥቅም እቅድ መግለጫ**

እርስዎ Wellpoint DC ልዩ የፋይናንስ ትብብር ከWellpoint DC ሐኪሞች ጋር ያላቸው መሆን ወይም አለመሆኑን የማወቅ መብት አለዎት።

እባክዎ ለዚህ መረጃ ወደ የWellpoint DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

## ***ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች***

Wellpoint DC እና የዲስትሪክቱ መንግስት ሁለቱም እርስዎ ስለሚያገኙት እንክብካቤ፣ ወይም Wellpoint DC ስለሚያቀርብልዎ አገልግሎቶች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ዘዴ አላቸው። ከታች እንደተገለጸው አቤቱታ እንዴት ማቅረብ እንዳለብዎት ሊመርጡ ይችላሉ።

### ቅሬታዎች

- እርስዎ ላይ በተፈጠረ አንድ ነገር ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። የሚከተሉት ቅሬታ ማቅረብ ሊያስፈልግዎ የሚችሉባቸው ምክንያቶችን ምሳሌ ያካትታሉ፥
    - በአክብሮት እንዳልተስተናገዱ ተሰምትዎታል
    - ባገኙት የጤና ሕክምና እንክብካቤ አልረኩም
    - ቀጠሮ ለማግኘት በጣም ረጅም ጊዜ ወስዷል
- ቅሬታ ለማቅረብ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ833-359-1384 (TTY 711) መደወል አለብዎት።
- በተጨማሪ ሐኪምዎ ለእርስዎ ቅሬታ ሊያቀርብልዎት ይችላሉ።

ያልተደሰቱበት ነገር ከተፈጠረ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። Wellpoint DC አብዛኛውን ጊዜ በ 90 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል ነገር ግን ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜም ሊጠይቁ ይችላሉ (ነገር ግን በአጠቃላይ ከ104 የካላንደር ቀናት ሊበልጥ አይችልም)።

ቅሬታ በጽሁፍ Wellpoint DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ለ Centralized Appeals Processing | Wellpoint District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

### ይግባኞች

ጥቅማጥቅሞችዎ አለአግባብ እንደተከለከሉ፣ እንደተቀነሱ፣ እንደዘገዩ፣ ወይም እንደቆሙ ከተሰማዎ፣ Wellpoint DC ጋር ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዎት። ደውለው ይግባኝዎን በስልክ ካቀረቡ፣ Wellpoint DC ይግባኝዎን በደብዳቤ አጠቃለው ይጽፉታል እና ለእርስዎ ቅጂውን ይልካሉ። ደብዳቤውን በጥንቃቄ ማንበብዎን እና ለመዝገቦችዎ ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

ይግባኝዎ በደረሰ በ 30 የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎ ላይ በWellpoint DC ውሳኔ ይሰጣል።

Wellpoint DC መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለጋቸው እና ዲስትሪክቱ ይህ ለእርስዎ የሚጠቅም እንደሆነ ከወሰነ፣ ወይም እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ ተጨማሪ ጊዜ ከጠየቃችሁ፣ Wellpoint DC የውሳኔ ጊዜውን በ 14 የካላንደር ቀናት ሊጨምረው ይችላል። Wellpoint DC ስለ ማራዘሚያው የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል።

ፖስታው ላይ፣ ስለ ይግባኝዎ የWellpoint DC የውሳኔ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።

Wellpoint DC በይግባኝዎ ላይ በሰጠው ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ፣ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።

Wellpoint DC ጋር ይግባኝ ለማቅረብ፣ ለተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ**833-359-1384 (TTY 711)** ይደውሉ።

ይግባኝን በጽሁፍ Wellpoint DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ወደ Centralized Appeals Processing | Wellpoint District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

### ፍትሃዊ ችሎቶች

እርስዎ Wellpoint DC ጋር ባቀረቡት ይግባኝ ውጤት ካልረኩ፣ የDC የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር "ፍትሃዊ ችሎት" መጠየቅ ይችላሉ።

የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄ ለማቅረብ፣ የዲስትሪክቱ መንግስት ጋር ይደውሉ ወይም ይጻፉ ወደ፥

District of Columbia Office of Administrative Hearings
Clerk of the Court
441 4th Street, NW
Room N450
Washington, DC 20001
የስልክ ቁጥር፥ 202-442-9094

**የመጨረሻ ቀናቶች፥**

- ጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ 60 የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎን ማቅረብ አለብዎት።
- የWellpoint DC የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን ከ120 የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- በፍትሃዊ ችሎትዎ ወይም ይግባኝዎ ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ማግኘት መቀጠል ከፈለጉ፣ ፍትሃዊ ችሎቱ ወይም የይግባኝ ችሎቱ ከሚከተለው ጊዜ በኋላ የሚከተሉትን እንዲያደርግልዎ መጠየቅ አለብዎት፥
  - በWellpoint DC የጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያን በላከበት ፖስታ ላይ ካለው ቀን ወይም የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን በ10 የካላንደር ቀናት፤ ወይም
  - የWellpoint DC የታቀደው እርምጃ ተፈጻሚነቱ ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ (ወይም፣ በሌላ አባባል፣ ጥቅማጥቅሙ የሚቆምበት ቀን)።

አቅራቢዎ እርስዎን በመወከል ይግባኝ ሊያቀርብልዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎት ሊጠይቅልዎ ይችላሉ።

**የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት**

ይግባኝዎ ድንገተኛ መሆኑ ከተወሰነ፣ Wellpoint DC በ 72 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል። አንድ ይግባኝ ድንገተኛ ነው ተብሎ የሚቆጠረው እርስዎ መደበኛውን የይግባኝ ሂደት የጊዜ ማዕቀፍ ቢጠብቁ ለእርስዎ ጎጂ ወይም የሚያሰቃይ ከሆነ ነው።

HIV/AIDS፣ የአእምሮ በሽታ፣ ወይም አፋጣኝ ትኩረት የሚፈልግ ሌላ ሁኔታ ባለባቸው ተመዝጋቢዎች የሚቀርቡ ሁሉም ይግባኞች ይግባኙ በቀረበ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ አግኝተው ለተመዝጋቢው ይገለጽላቸዋል።

**በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሎት መብቶች**

- እርስዎ ፍትሃዊ ችሎት የማግኘት መብት አለዎት። እርስዎ Wellpoint DC ጋር አንድ ደረጃ ያለው የይግባኝ ሂደት ካቀረቡ በኋላ፣ ከአስተዳደራዊ ችሎት ቢሮ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን አንስቶ ከ 120 የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ አለብዎት።
- Wellpoint DC ይግባኝዎን የሚመለከት ማስታወቂያ ካልሰጠዎት ወይም በጊዜ ማስታወቂያ ካልሰጠዎት፣ ከዚያ በኋላ የይግባኝ ሂደቱ የተሟላ እንደሆነ ይቆጠራል፣ እና ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ይግባኝዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ በሚታይበት ጊዜ የከለከልንዎትን ጥቅማጥቅም እያገኙ የመቆየት መብት አለዎት። በፍትሃዊ ችሎት ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ይዞ ለመቆየት፣ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ፍትሃዊ ችሎቱን መጠየቅ አለብዎ - ይህ ጊዜ ከ 10 የካላንደር ቀናት ያጠረ ሊሆን ይችላል።
- እርስዎ በቅሬታ እና የይግባኝ ሂደት ወቅት ከWellpoint DC አንድ ሰው እርዳታ የማግኘት መብት አለዎት።
- እራስዎን የመወከል ወይም በቤተሰብ ተንከባካቢ፣ ጠበቃ፣ ወይም ሌላ ወኪል የመወከል መብት አለዎት።
- ለማንኛውም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች መቆያ እንዲመቻችልዎ የመጠየቅ መብት አለዎት።

- እርስዎ በቂ የ TTY/TTD ችሎታዎች እና ማየት ለተሳናቸው አገልግሎቶች የማግኘት መብት አሎት።
- እርስዎ በቂ የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አለዎት።
- እርስዎ ከቅሬታዎ፣ ይግባኝዎ፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ሰነዶች የማየት መብት አለዎት።

ስለ ቅሬታዎቹ እና ይግባኞቹ/ፍትሃዊ ችሎት ሂደት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ**833-359-1384 (TTY 711)**።

<u>የግላዊነት ልምምዶች ማስታወቂያ</u>

***እባክዎ ይህን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡ። ይህ የእርስዎን የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) ማን ማየት እንደሚችል ይነግርዎታል። እኛ ከማጋራታችን በፊት ይሁንታዎን መቼ መጠየቅ እንዳለብን ይነግርዎታል። ይሁንታዎ ሳይኖር መቼ ማጋራት እንደምንችል ይነግርዎታል። በተጨማሪ የእርስዎን መረጃ ለማየት እና ለመለወጥ ያሎት መብቶች ምን እንደሆኑ ይነግርዎታል።***

ስለ ጤናዎ እና ስለ ገንዘብዎ ያለው መረጃ ሚስጥራዊ ነው። ሕጉ ደህንነቱ የሚጠበቅ የጤና መረጃ (PHI) በመባል የሚጠራውን ይህን ዓይነት መረጃን፣ ለአባሎቻችን ደህነነቱ በጠበቀ መልኩ እንድንጠብቅ ያስገድደናል። ያ ማለት እርስዎ አሁን አባል ከሆኑ ወይም ከዚህ በፊት አባል ከነበሩ፣ የመረጃዎ ደህንነት የተጠበቀ ነው ማለት ነው።

ለጤና እቅዳችን ብቁ ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ፣ ለMedicaid እና የህጻናት የጤና መድን ፕሮግራም ከስቴት ኤጀንሲዎች ስለእርስዎ መረጃ እናገኛለን። በተጨማሪም ለጤና እንክብካቤዎ እንድንፈቅድ እና ክፍያ እንድንፈጽም፣ ከእርስዎ ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች፣ የምርመራ ቤቶች፣ እና ሆስፒታሎች መረጃ እናገኛለን።

የፌደራል ህግ በጽሁፍ የተነገረንን ወይም በኮምፒዩተር የተቀመጠን PHI ለመጠበቅ ህጉ እንድናደርጋቸው ስለሚያዛቸው ነገሮች ለእርስዎ መንገር እንዳለብን ያስገድደናል። በተጨማሪ እኛ ደህንነቱን እንዴት እንደምንጠብቅ ልንነግርዎ ይገባል። PHIን ለመጠበቅ፦
- በወረቀት ላይ (ቁሳዊ ተብሎ የሚጠራ)፣ እኛ፦
  - ቢሮዎቻችንን እና ፋይሎቻችንን እንቆልፋለን
  - ሌሎች እንዳያገኙት የጤና መረጃ የያዙ መረጃዎችን እናስወግዳለን
- በኮምፒውተር ላይ የተቀመጠ (ቴክኒካል ተብሎ የሚጠራው)፣ እኛ፦
  - ትክክለኛዎቹ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ የይለፍ ቃሎችን እንጠቀማለን
  - ሲስተሞቻችንን ለመከታተል ልዩ ፕሮግራሞችን እንጠቀማለን
- ለእኛ፣ ለሐኪሞች ወይም ለዲስትሪክት የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቀሙት ወይም የሚያጋሩት፣ እኛ፥
  - የመረጃ ደህንነትን ለመጠበቅ መመሪያዎችን እናወጣለን (ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓቶች ተብለው ይጠራሉ)
  - ለእኛ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያዎቹንን እንዲከተሉ እናስተምራቸዋለን

**እኛ የእርስዎን PHI መጠቀም እና ማጋራት የምንችለው መቼ ነው?**
የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን የእርስዎን PHI ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎት ለመረጡት ሰው ልናጋራ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፣ ***ያለእርስዎ*** ይሁንታ ልንጠቀምበት እና ልናጋራው እንችላለን፥
- **ለህክምና እንክብካቤዎ**
  - ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች እርስዎ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንዲሰጡ ለመርዳት
- **ለክፍያ፣ የጤና እንክብካቤ ስራዎች እና ህክምና**
  - ለእርስዎ እንክብካቤ ክፍያ ከሚጠይቁን ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጋር መረጃ ለመጋራት።
  - የጤና እንክብካቤ ወይም አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት እንደምንከፍልልዎት ከተናገርን
  - ፕሮግራሞቻችንን የተሻሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን ለማግኘት፣ እንዲሁም የእርስዎን PHI ለጤና መረጃ ልውውጥ ማጋራት ለክፍያ፣ ለጤና እንክብካቤ ስራዎች እና ለህክምና። ይህንን የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን ለበለጠ መረጃ **wellpoint.com/dc/medicaid** ይጎብኙ።

- **ለጤና አጠባበቅ ጉዳይ ምክንያቶች**
  - የኦዲት፣ ማጭበርበር እና አላግባብ መጠቀምን የመከላከል ፕሮግራሞችን፣ እቅድ ማውጣትን እና የዕለት ተዕለት ሥራን ለመርዳት
  - ፕሮግራሞቻችንን የተሻሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን ለማግኘት
- **ለሕዝብ ጤና ምክንያቶች**
  - የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ሰዎችን ከመታመም ወይም ከመጎዳት እንዲጠብቁ ለመርዳት
- **ለእንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርጉ ወይም ለሚከፍሉ ሌሎች ሰዎች ጋር**
  - የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን፣ ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎት ወይም ለሚከፍልልዎት ለመረጡት ሰው ጋር
  - ስለራስዎ መናገር የማይችሉ ከሆነ እና ለእርስዎ የተሻለ ከሆነ፣ ለጤና እንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርግልዎት ወይም ለሚከፍልልዎት ሰው ጋር

ለሕክምናዎ፣ ክፍያ፣ የእለት ተለት ሥራ፣ የምርምር ጥናት ወይም ከታች ለተዘረዘሩት ሌሎች ነገሮች ውጪ የእርስዎን PHI ከመጠቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታ በጽሁፍ ማግኘት አለብን። ስለ እርስዎ ከሐኪምዎ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን የጽሁፍ ይሁንታ ማግኘት አለብን።
በጽሁፍ የሰጡትን ይሁንታን መተው እንደሚፈልጉ በጽሁፍ ሊነግሩን ይችላሉ። የእርስዎ ይሁንታ ባለበት ወቅት የተጠቀምነውን ወይም ያጋራነውን መመለስ አንችልም። ነገር ግን ወደፊት የእርስዎን PHI መጠቀም ወይም ማጋራት እናቆማለን።

**ሌሎች መንገዶች - ወይም ህጉ የሚፈቅድልን - የእርስዎን PHI እንድንጠቀም፥**

- ፖሊስን እና ሌሎች ህግ የሚያስከብሩ ሰዎችን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ አላግባብ መጠቀምን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ PHI ን ልንጠቀም እንችላለን።
- ስንጠየቅ ፍርድ ቤቱን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ በፍርድ ቤት የሚያያዙ እንደ አቤቱታ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ የመሳሰሉ ህጋዊ ሰነዶች ላይ ምላሽ ለመስጠት PHI ልንጠቀም እንችላለን።
- ለጤና ቁጥጥር ኤጀንሲዎች ወይም ለሌሎች ለመንግስት አንዳንድ ስራዎችን ለሚሰሩ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ ለኦዲት ወይም ለፈተና መረጃ እንሰጣለን።
- የእርስዎን ስም እና የሞት መንስኤ ለማወቅ እንዲረዳቸው ለሬሳ ምርመራ ሐኪሞች፣ የህክምና መርማሪዎች ወይም የቀብር አስፈጻሚዎች።
- የሰውነት ክፍሎችዎን ለሳይንስ ወይም ለጥናት ምርምር ለመስጠት ሲጠይቁ ለመርዳት። ለምሳሌ፣ ሲሞቱ የሰውነት ክፍልዎን ለመለገስ ከተስማሙ መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን።
- እርስዎን ወይም ሌሎች ከመታመም ወይም ከፉኛ ከመጎዳት ለመጠበቅ። ለምሳሌ፣ እርስዎ ወይም ሌሎች በአስቸኳይ ሁኔታ ውስጥ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ለመከላከል የእርስዎን PHI ልናጋራ እንችላለን።
- ለሠራተኞች ካሳ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ በስራ ላይ ሆነው ከታመሙ ወይም ከተጎዱ የእርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

***መብቶችዎ ምንድን ናቸው?***

- የእርስዎን PHI ለማየት እና ቅጂውን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን መሉ የሕክምና መረጃዎ የለንም። ሙሉ የህክምና መረጃዎን ቅጂ ከፈለጉ፣ ሐኪምዎን ወይም የጤና ክሊኒክዎን ይጠይቁ።
- የሆነ ችግር አለ ወይም የጎደለ ነገር አለ ብለው ካሰቡ ያለንን የእርስዎን የሕክምና መረጃ እንድንቀይረው እኛን መጠየቅ ይችላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ የእርስዎን PHI እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ነገር ግን በጥያቄዎ የግድ መስማማት የለብንም ። ለምሳሌ፣ PHI የክሊኒካል ማስታወሻዎች አካል ከሆነ እና በህግ ሊለቀቅ የማይችል ከሆነ ጥያቄዎ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።
- ካለን የእርስዎ አድራሻ ውጪ ወዳለ አድራሻ ወይም በተወሰነ ሌላ መንገድ PHI እንድንልክልዎ እኛን መጠየቅ ይችላሉ። ባለን የእርስዎ አድራሻ መላክ እርስዎን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ይህን ማድረግ እንችላለን።
- ባለፉት ስድስት ዓመታት የእርስዎን PHI ለሌላ ሰው ያጋራንበትን ሁሉንም መረጃ እንድንነግርዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህ ለጤና እንክብካቤ፣ ለክፍያ፣ ለዕለትተዕለት የጤና እንክብካቤ ሥራ ወይም እዚህ ባልዘረዘርናቸው ሌሎች ምክንያቶች ያጋራንበትን ጊዜ አያካትትም።
- የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በኢሜይል እንዲላክልዎ የጠየቁ ቢሆንም እንኳን የወረቀት ቅጂ እንዲላክልዎ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአንድ አገልግሎት ሙሉዉን ክፍያ ከከፈሉ፣ ስለዚያ አገልግሎት መረጃውን ለእኛ እንዳያጋሩ ሐኪምዎን መጠየቅ ይችላሉ።

**እኛ ምን ማድረግ አለብን?**

- ህጉ በዚህ ማስታወቂያ ከገለጽነው ውጪ የእርስዎን PHI ሚስጥራዊ ማድረግ እንዳለብን ያስገድዳል።
- ህጉ ስለ ሚስጥራዊነት እንድናደርግ የሚያስገድደን ምን እንደሆነ ለእርስዎ መንገር አለብን።
- በዚህ ማስታወቂያ እናደርጋለን ብለን የገለጽናቸውን ነገሮች ማድረግ አለብን።
- እርስዎ ከጠየቁ እና አደጋ ላይ ከሆኑ፣ የእርስዎን PHI ወደ ሌላ አድራሻ ወይም መደበኛ ከሆነው ፖስታ ውጪ በሌላ መንገድ መላክ አለብን።
- እንዳናጋራው ከነገሩን በኋላ የእርስዎን PHI ማጋራት ካለብን ለእርስዎ መንገር አለብን።
- እኛ እዚህ እናደርጋቸዋለን ብለን ከገለጽናቸው በላይ የስቴት ህጎች ማድረግ እንዳለብን የሚያስገድዱ ከሆነ፣ እነዚያን ህጎች እንከተላለን።
- የእርስዎ PHI እንደተጣሰ ካሰብን እኛ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።

**እኛ ልናገኝዎት እንችላለን**

እኛ፣ ተባባሪዎቻችን እና/ወይም አቅራቢዎቻችንን ጨምሮ፣ አውቶማቲክ የስልክ መደወያ ስርዓት እና/ወይም ቀድሞ የተቀዳ መልእክትን በመጠቀም፣ ገመድ አልባ የስልክ ቁጥርን ጨምሮ ወደሚሰጡን ማንኛውም የስልክ ቁጥሮች ላይ እንድንደውል ወይም የጽሁፍ መልእክት እንድንልክ ተስማምተዋል። እነዚህ የስልክ ጥሪዎች ወይም የጽሁፍ መልእክቶች ስለህክምና አማራጮች፣ ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞች እና አገልግሎቶች፣ ምዝገባ፣ ክፍያ፣ ወይም የክፍያ መጠየቂያ ሊሆኑ የሚችሉ ስሊሆን ነገር ግን በዚህ የተገደቡ አይደሉም።

**ጥያቄዎች ካሉዎትስ?**

ስለ የኛ የሚስጥራዊነት መመሪያችን ጥያቄዎች ካሎት ወይም መብቶችዎን መጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ833-359-1384 ይደውሉ። መስማት የተሳነዎ ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት፣ ይደውሉ TTY 711።

**ቅሬታ ካለዎትስ?**

እኛ እዚህ ያለነው ለማገዝ ነው። የእርስዎ PHI ደህንነቱ እንዳልተጠበቀ ከተሰማዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ወይም የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን ማግኘት ይችላሉ።

**ለጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ይጻፉ ወይም ይደውሉ፥**

Office for Civil Rights
U.S. Department of Health and Human Services
200 Independence Ave. SW
Washington, DC 20201
ስልክ፥ 800-368-1019
TDD፥ 800-537-7697

ይህን የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ማስታወቂያ እና የእርስዎን PHI ደህንነት የምንጠብቅባቸውን መንገዶች የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። እንዲያ ከሆነ፣ እኛ ስለለውጦቹ በመጽሄቶች እንነግርዎታለን። በተጨማሪም በድረገጽ በ **wellpoint.com/privacy** ላይ እንለጥፋቸዋለን።

**ዘር፣ ብሄር እና ቋንቋ**

እኛ ስለ እርስዎ የዘር፣ የብሄር እና የቋንቋ መረጃ ከስቴት የMedicaid ኤጀንሲ እና ከልጆች የጤና መድን ፕሮግራም እናገኛለን። ይህን መረጃ በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተገለጸው እንጠብቀዋለን።
ይህንን መረጃ ለሚከተሉት እንጠቀማለን፥

- የሚያስፈልግዎትን መረጃ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ
- የጤና ውጤቶችን የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን ለመፍጠር
- የጤና ትምህርት መረጃ ለማዘጋጀት እና ለመላክ
- ስለ ቋንቋ ፍላጎቶችዎ ለሐኪሞች ለማሳወቅ
- የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለመስጠት

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት **<u>እንጠቀምበትም</u>**፥
- የጤና መድን ለመስጠት
- ለአገልግሎቶች ምን ያክል ለማስከፈል ለመወሰን
- ጥቅማጥቅሞችን ለመወሰን
- ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ለመግለጽ

**የግል መረጃዎ**

የስቴት ህጎች የHIPAA የግላዊነት መመሪያ ላይ ካለው በላይ ግዴታ የሚጥሉብን ከሆነ ያንን እናከብራለን። በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተናገርነው የግል መረጃን (PI) ልንጠይቅ፣ ልንጠቀም እና ልናጋራ እንችላለን። የእርስዎ PI ለህዝብ ይፋ አይደለም እና እርስዎ ማን እንደሆኑ ይነግረናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚወሰደው ለመድን ዓላማ ነው።
- የእርስዎን PI ስለእርስዎ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ለመወሰን ልንጠቀም እንችላለን፥
  - ጤና
  - ልማዶች
  - የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች
- ስለ እርስዎ PI ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ልናገኝ እንችላለን ለምሳሌ፥
  - ሐኪሞች
  - ሆስፒታሎች
  - ሌሎች የመድን ኩባንያዎች
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የእርስዎን ይሁንታ ሳናገኝ ከኩባንያችን ውጪ ላሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች PI ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ስራችንን ለማስኬድ እንዲረዱን ከምንቀጥራቸው የይገባኛል ጥያቄዎች እና የሂሳብ አከፋፈል አቅራቢዎች ጋር PI ልናጋራ እንችላለን።
- ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የመከልከል እድል ለእርስዎ ለመስጠት እናሳውቅዎታለን።
- የእርስዎን PI እንድንጠቀም ወይም እንድናጋራ ካልፈለጉ ለኛ እንዴት እንደሚያሳውቁን እንነግርዎታለን።
- የእርስዎን PI የማየት እና የመቀየር መብት አሎት።
- የእርስዎ PI ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እናረጋግጣለን።

**የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ**

የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ፕሮግራም ከእርስዎ MCP የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ እርስዎን የሚያግዝ የColumbia ዲስትሪክት መንግስት ፕሮግራም ነው። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፥

- ማግኘት የሚገባዎን የጤና እንክብካቤ መብት ማብራራት፤
- የጤና እንክብካቤዎን የሚመለከቱ ጥያቄዎችዎን እና ስጋቶችዎ ላይ ምላሽ መስጠት፤
- የMCP ተመዝጋቢ በመሆንዎ ያሎትን መብቶች እና ግዴታዎችን እንዲረዱ ማገዝ፤
- የሚያስፈልግዎትን አስፈላጊ የሕክምና አገልግሎቶች እንዲያገኙ እርዳታ መስጠት።
- የጤና እንክብካቤዎ ጥራትን በሚመለከት ሊኖርዎ የሚችሉ ጥያቄዎችን እና ስጋቶችን መመለስ።
- ከሐኪምዎ ጋር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ያለብዎትን ችግሮች እንዲፈቱ ማገዝ።
- ከMCP ጋር ያሉ አቤቱታዎችን እና ችግሮችን ለመፍታት እርዳታ መስጠት፤
- የይግባኝ ሂደቶች ላይ ማገዝ፤ እና
- ፍትሃዊ ችሎት ለማቅረብ ለእርስዎ ለመጠየቅ እርዳታ መስጠት

የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቶች ላይ ውሳኔ አይሰጥም። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂን ለማግኘት፣ እባክዎ በ202-724-7491 ወይም 877-685-6391 (ከክፍያ ነጻ) ይደውሉ። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ የሚገኘው በ፥

One Judiciary Square
441 4th Street, NW
Suite 250 North
Washington, DC 20001
**ስልክ፥** 202-724-7491
**ፋክስ፥** 202-442-6724
**ከክፍያ ነጻ ቁጥር፥** 877-685-6391
**ኢሜይል፥** healthcareombudsman@dc.gov

**ትርጉሞች**

| | |
|---|---|
| **የቅደም መመሪያ** | እርስዎ በጣም ከታመሙ ወይም ከተጎዱ እና ስለራስዎ መናገር ባይችሉ ሌሎች ስለሚፈልጉት እና የማይፈልጉት የጤና እንክብካቤ እንዲያዉቁ የሚያደርግ በጽሁፍ የሆነ፣ በእርስዎ የተፈረመ ህጋዊ ወረቀት ነው። |
| **ጠበቃ** | እርስዎ የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያግዝዎ ሰው። |
| **ይግባኝ** | ይግባኝ ማለት Wellpoint DC የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን ወይም ላገኟቸው አገልግሎቶች ክፍያ በመከልከል በሚሰጠው አንድ ውሳኔ ሳይስማሙ ሲቀር የሚያቀርቡት ልዩ አቤቱታ ነው። በተጨማሪ በውሳኔው ካልተስማሙ እያገኙ ያሉትን አገልግሎቶች ለማስቆም ይህን ዓይነት ልዩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **ቀጠሮ** | የጤና ሕክምና ፍላጎቶችዎ ላይ እርስዎ እና ሐኪምዎ ለመወያየት የሚወስኑት የተወሰነ ጊዜ እና ቀን ነው። |
| **የባህሪይ ጤና** | የአእምሮ ጤና ሁኔታዎች (የአእምሮ ሕመሞችን እና የስሜት መቃወስን ጨምሮ) እና የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መዛባት (ሱስ እና ኬሚካላዊ ጥገኝነት መታወክን የሚያካትቱ) ጃንጥላ ቃል። ቃሉ እንዲሁ አብሮ የሚመጡ የአእምሮ ጤና ሁኔታዎችን እና የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መዛባትን (SUDS) መከላከል እና ማከምን ያመለክታል። |
| **የሕክምና አስተዳዳሪ** | የሚያስፈልግዎትን ሕክምና፣ ድጋፍ፣ እና ጤናማ ሆነው ለመቆየት የሚያስፈልግዎትን መረጃ እንዲያገኙ እርስዎን ለመርዳት ከWellpoint DC ጋር የሚሰራ ሰው ነው። |
| **ምርመራ** | *የማጣሪያ ምርመራን ይመልከቱ* |
| **የወሊድ መቆጣጠሪያ** | የወሊድ መቆጣጠሪያ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች |
| **ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በWellpoint DC ክፍያ የሚከፈልባቸው። |
| **መርዛማ ነገር ከሰውነት ውስጥ ማስወጣት** | እንደ አደንዛዥ እጽ እና የአልኮል መጠጥ የመሳሰሉ ጎጂ ነገሮችን ከሰውነት ማስወገድ። |
| **እድገት** | ልጅዎ እንዴት እንደሚያድግ። |
| **የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም** | ከባድ በሽታ ያለባቸው ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ የመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና የሚፈልጉ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚረዳ ፕሮግራም። |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)** | ቤትዎ ውስጥ እንዲጠቀሙት ሐኪምዎ የሚጠይቅዎ ወይም የሚያዝዎ ልዩ የሕክምና መሳሪያ። |
| **የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና** | ለከባድ፣ ድንገተኛ፣ አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ ለሆነ ሁኔታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ ሕክምና። |
| **ተመዝጋቢ** | በWellpoint DC አገልግሎት አቅራቢ አውታረመረብ በኩል የጤና እንክብካቤ የሚያገኘው ሰው። |
| **የተመዝጋቢ የመለያ (ID) ካርድ** | እርስዎ የWellpoint DC ተመዝጋቢ መሆንዎን ሐኪሞችዎ፣ ሆስፒታሎች፣ መድሃኒት ቤቶች፣ እና ሌሎች እንዲያውቁት የሚያደርግ ካርድ። |
| **EPSDT**<br>**የቅደመ፣ በየጊዜው የሚደረግ ማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና የሕክምና አገልግሎቶች ፕሮግራም** | ከልደት እስከ 21 እድሜ ያሉ ልጆች የሕክምና ምርመራዎች፣ የክትትል ምርመራዎች፣ የክትትል ሕክምና፣ እና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አገልግሎቶች። እንዲሁም የ *HealthCheck Benefit* በመባልም ይታወቃል። |
| **ፍትሃዊ ችሎት** | ይግባኝዎ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ የDC የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። |

| | |
|---|---|
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | አገልግሎቶቹ የእርግዝና ምርመራዎች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ እና የHIV/AID ምርመራ እና የምክር አገልግሎትን ያካትታል። |
| **የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሕክምና ሐኪም** | መላውን ቤተሰብ ሊያክም የሚችል ሐኪም። |
| **ቅሬታ** | በሚያገኙት ሕክምና፣ ወይም Wellpoint DC በሚሰጠው የጤና ሕክምና አገልግሎቶች ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ለማቅረብ የተመዘጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ። |
| **የመመሪያ መጽሃፍ** | ይህ መጽሀፍ ስለ Wellpoint DC እና ስለኛ አገልግሎቶች መረጃ ይሰጥዎታል። |
| **HealthCheck ፕሮግራም** | *ይመልከቱ EPSDT* |
| **መስማት የተሳነው** | በሚገባ መስማት የማይችሉ ከሆነ ወይም መስማት የተሳኖት ከሆኑ |
| **IDEA** | የአካል ጉድለት ያለባቸው ሰዎች የትምህርት ህግ፤ የእድገት መዘግየት እና ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎት ላላቸው ልጆች አገልግሎት የሚሰጥ የፌደራል ህግ ነው። |
| **ክትባት** | መርፌ ወይም ክትባት። |
| **የውስጥ ደዌ ሕክምና ሐኪም** | የአዋቂዎች እና እድሜያቸው ከ 14 ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ሐኪም። |
| **የአስተርጓሚ/የትርጉም አገልግሎቶች** | የራስዎን ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ለማውራት ወይም ከሐኪምዎ ጋር ወይም ከሆስፒታሉ ጋር ለማውራት ከWellpoint DC የሚያገኙት እርዳታ። |
| **የሚተዳደር እንክብካቤ እቅድ (MCP)** | እርስዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና ሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የColumbia ዲስትሪክት የሚከፍለው ኩባንያ። |
| **የወሊድ ጊዜ** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና የምትቆይበት እና ከወሊድ በኋላ ያለው አጭር ጊዜ። |
| **የአእምሮ ጤና** | አንድ ሰው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያስበው፣ የሚሰማው፣ እና የሚያደርገው ድርጊት። |
| **የመረብ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ እና የWellpoint DC አካል የሆኑ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለተሰጠ የጤና ሕክምና Wellpoint DC ክፍያ የማይፈጽምበት። |
| **OB/GYN** | አዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም፤ እርግዝናን ጨምሮ፣ የሴት ጤናን ለማከም የሰለጠነ ሐኪም። |
| **ከአውታረ-መረብ ውጭ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ እና የWellpoint DC አካል **ያልሆኑ** ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **የህጻናት ሀኪም** | የልጆች ሐኪም። |
| **መድሃኒት ቤት** | መድሃኒትዎን የሚያገኙበት ቦታ። |
| **የሐኪም የጥቅማጥቅም እቅድ** | ሐኪምዎ ከWellpoint DC ጋር ማንኛውም ልዩ ትብብር ካላቸው ይነግርዎታል። |
| **የድህረ ወሊድ ሕክምና** | ልጅዎን ከወለደች በኋላ አንዲት ሴት የምታገኘው የጤና ሕክምና ነው። |
| **የቅድመ ወሊድ ሕክምና** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና በምትቆይበት ጊዜ ሁሉ የሚሰጥ የሕክምና እንክብካቤ ነው። |
| **የመድሃኒት ማዘዣ** | ሐኪምዎ ለእርስዎ የሚያዙት መድሃኒት፤ መድሃኒቱን ለማምጣት ወደ መድሃኒት ቤት መውሰድ አለብዎ። |
| **የመከላከል የምክር አገልግሎት** | ጤናማ ሆነው ለመቆየት ወይም ከመታመም ወይም ከመጎዳት እራስዎን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ዘዴዎች ከአንድ ሰው ጋር ማውራት ሲፈልጉ። |
| **ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)** | አብዛኛውን ጊዜ ለእርስዎ ሕክምና የሚሰጡት ሐኪም። |
| **ቅድመ ፈቃድ** | የጤና እንክብካቤ ወይም ህክምና ለማግኘት ከWellpoint DC የጽሁፍ ፍቃድ። |
| **የአቅራቢ ማውጫ** | የWellpoint DC  አካል የሆኑ ሁሉም አቅራቢዎች ዝርዝር። |
| **አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |

| | |
|---|---|
| **ሪፈራል** | በሌላ ሐኪም እንዲታዩ እርስዎን ለመላክ ዋና ሐኪምዎ የሚሰጠው የጽሁፍ ማስታወሻ። |
| **መደበኛ ህክምና** | ከዋና የሕክምና አቅራቢዎ ወይም ዋና የሕክምና አቅራቢዎ ከላከዎ ሐኪም የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና። መደበኛ የሕክምና ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ማጣሪያ ምርመራ፣ እና እንደ የስኳር በሽታ፣ አስም፣ እና የደም ግፊት የመሳሰሉ የጤና ችግሮችን በተመለከተ የሚያገኙት መደበኛ ሕክምናን ያካትታል። |
| **የማጣሪያ ምርመራ** | እርስዎ ጤናማ መሆንዎን ለማወቅ ሐኪምዎ ወይም ሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ ሊያከናውኑት የሚችሉ ምርመራ። ይህ የመስማት፣ የእይታ፣ ወይም ልጅዎ መደበኛ እድገቱን እያከናወነ መሆኑን ለማየት የሚደረግ ምርመራ ሊሆን ይችላል። |
| **የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች** | ከዋና ሐኪምዎ የጽሁፍ ማስታወሻ ወይም ሪፈራል ሳያስፈልግዎ ሊያገኟቸው የሚችሉ የተወሰኑ አገልግሎቶች። |
| **አገልግሎቶች** | ከሐኪምዎ ወይም ከሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ የሚያገኙት ሕክምና። |
| **ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች** | ሌሎች ልጆች ወይም አዋቂዎች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ወይም የተለየ የጤና ሕክምና እና ሌሎች ልዩ አገልግሎቶች የሚፈልጉ ልጆች እና አዋቂዎች። |
| **ስፔሺያሊስት** | ልዩ ሕክምና ለመስጠት የሰለጠነ ሐኪም፥ እንደ የጀሮ፣ የአፍንጫ፣ የጉሮሮ፣ ወይም የእግር ሐኪም። |
| **የስፔሺያሊቲ ሕክምና** | የጤና ሕክምናው የሚሰጠው ልዩ ዓይነት የጤና ሕክምና ለመስጠት በሰለጠኑ ሐኪሞች ወይም ነርሶች ነው። |
| **የማምከን ሕክምናዎች** | ልጅ መውለድ ወደፊት ሳይፈልጉ ሲቀር ሊያደርጉት የሚችሉት የቀዶ ጥገና። |
| **የሱስ አጠቃቀም በሽታ (SUD)** | በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀም የሚሰቃይ በሽተኛ አያያዝ እና እንክብካቤ፣ ይህ በመጠቀም የተከሰተ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ነው። |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ ቀጠሮ ቦታዎ ለመሄድ ከWellpoint DC እርዳታ። የሚያገኙት የትራንስፖርት ዓይነት የሚወሰነው በሚያስፈልግዎ የሕክምና ዓይነት ነው። |
| **ሕክምና** | ከሐኪምዎ የሚያገኙት ሕክምና። |
| **አስቸኳይ ህክምና** | ወዲያውኑ ሳይሆን፣ በ24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ ሕክምና። |
| **ማየት የተሳነው** | በሚገባ ማየት የማይችሉ ከሆነ ወይም ማየት የተሳኖት ከሆነ። |

ሽፋን የቀረበው በWellpoint District of Columbia, Inc. ነው።

Wellpoint
District of Columbia


የተመዝጋቢ አገልግሎቶች፥
609 H St. NE, Suite 200
Washington, DC 20002

**202-548-6700**
**833-359-1384 (TTY 711)** (ከክፍያ-ነፃ)

**wellpoint.com/dc/medicaid**


DHCF Department of Health Care Finance

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is brought to you by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

1046355DCMAMWLP 03/25